# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 322 ሐምሌ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ትግበራ ገባች

## - አስፈላጊ የደመወዝ ድጎማና ማሻሻያዎች ይደረጋሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ትግበራ መግባቷን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስታወቀ። ማሻሻያው በወሳኝ የልማት አጋሮች እንደሚደገፍና አስፈላጊ የደመወዝ ድጎማና ማሻሻያዎች እንደሚደረጉ ተገልጿል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ትናንትና ባወጣው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም የፖሊሲ መግለጫ የ2010 ዓ.ም የፖለቲካ ለውጥን ተከትሎ መንግሥት አያሌ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተግባራትን ማከናወኑን አስታውሷል።

በ2011 በጀት ዓመት ወደ ትገበራ የገባው የመጀመሪያው ምዕራፍ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ብዙ የፖሊሲ ሀሳቦችን በውስጡ ያካተተ እና መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ ዓላማዎችንና ግቦችን ያሳካ እንደነበር ተመላክቷል።

የፖሊሲና የሕግ ማሻሻያ ሂደቶቹ ኢኮኖሚው ወደ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ እንዲሸጋገር አዲስ ተስፋን ማምጣታቸው ተብራርቷል።

ቀሪ ሥራዎች ቢኖሩም፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን መዛባትን ለማረም፣ የዕዳ ጫናን ለማቃለል፣ የሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለማሳደግ፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮችን ለማስፋፋት፣ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር እና መዋቅራዊ ማነቆዎችን ለማረም በተደረገው ጥረት ውጤቶች መገኘታቸው

ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል














ኮሚሽነር መላኩ ወልደማሪያም

# በጋምቤላ

## ዛሬ የሚጀመረው የአጀንዳ ማሰባሰብ ለሀገራዊ መግባባት ሂደቱ ወሳኝ ምዕራፍ ነው

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በጋምቤላ ክልል ዛሬ የሚጀመረው የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ ለሀገራዊ መግባባት ሂደቱ ወሳኝ ምዕራፍ መሆኑን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ።

በጋምቤላ ዛሬ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



# የምርምር ጥራትን ለማሳደግ የሚረዱ ቴክኖሎጂዎች

**ዜና ትንታኔ**
**ሄለን ወንድምነው**

ፕላጃሪዝም የምረቃ ጽሑፍ የሚያዘጋጅና የምርምር ሥራ የሚሠራ ሰው ሌሎች ሰዎች የሠሩትን ሥራ የራሱ እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ እንዲሁም የአካዳሚክና የምርምር ሕግጋትን በመጣስ የሚፈፅመው

የምርምር ጥራትን ... ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# የሆርቲካልቸር ማነቆዎችና ምርታማነቱን የማሳደግ ትልም

**ዜና ትንታኔ**
**ፋንታነሽ ክንዴ**

ኢትዮጵያ ከሆርቲካልቸር ዘርፉ በየዓመቱ በአማካይ ከ500 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ታገኛለች፡፡ ለ200 ሺህ ዜጎችም የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ኢትዮጵያ በዘርፉ ካላት አቅም አንጻር አሁንም ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅ የዘርፉ ተዋናዮች ይገልጻሉ፡፡

የሆርቲካልቸር ማነቆዎችና ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል








# ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ከ60 ሺህ ሔክታር በላይ መሬት ተላልፏል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት 60 ሺህ 729 ሔክታር መሬት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች መተላለፉን በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት የግብዓት ክላስተር፣ የፋይናንስና ጉምሩክ ክላስተር አስተባባሪ ታደለ አስማረ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ምቹ የሆነ የኢንዱስትሪ ዞን ለመፍጠር ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የለማ መሬት የማቅረብ ሥራ ተከናውኗል።

60 ሺህ 729 ሔክታር መሬት ተዘጋጅቶ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች መቅረቡን አስታውቀው፤ የአምራች ኢንዱስትሪዎች መሠረተ ልማትን ከማሟላትና ከማነቃቃት አንጻር ጥሩ አፈጻጸም መታየቱን ተናግረዋል።

ከቀረበው መሬት ውስጥ 24 ሺህ ሔክታር የሚሆነው መሬት የለማና ከሦስተኛ ወገን ነፃ ሆኖ ለባለሀብቶች የተላለፈ መሆኑን ተናግረዋል። ይህም ከ 2015 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከሦስት እጥፍ በላይ መሻሻል የታየበት መሆኑን አንስተዋል፡፡

ክልሎች ለኢንዱስትሪ መስፋፋት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ቅድሚያ ሰጥተው በመሥራታቸውና በተሻለ አቅም የመሬት ዝግጅት በማድረጋቸው ውጤት መመዝገቡን ገልጸዋል፡፡ ይህም አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን ተናግረዋል፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪው ላይ በርካታ የመሠረተ ልማት ችግሮች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በተለይም የለማ መሬትና የኃይል አቅርቦት፣ የውሃና የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች ላይ በሰፊው ጥያቄ ይነሳል ብለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ትኩረት መስጠቱን አመላክተዋል።

ሌላኛው ምቹ የሆነ ኢንዱስትሪ ዞንን ለመፍጠር ከተሠሩ ሥራዎች መካከል የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ማሻሻል አንዱ መሆኑን አስተባባሪው አስረድተዋል።

በርካታ ኢንዱስትሪዎች የቆጣሪና የኃይል ማሻሻያ ጥያቄ አቅርበው እንደነበር አስታውሰው፤ ለተመረጡ ለአንድ ሺህ 777 አምራቾች ኃይል እንዲቀርብ መደረጉን ገልጸዋል። አፈጻጸሙ ጥሩ ቢባልም በዘርፉ ላይ አሁንም በርካታ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡

አስተባባሪው እንዳስታወቁት፤ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚውሉ 37 አዳዲስ የኤሌክትሪክ ትራንስፎርመሮችን በማስገባት እንዲሁም ሦስት ሺህ 397 ትራንስፎርመሮችን በመጠገን ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

ሌላኛው ጽሕፈት ቤቱ ማሻሻያ ካደረገባቸው መሠረተ ልማቶች አንዱ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ መሆኑን አንስተው፤ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በዘርፉ የሚያጋጥሙ የተለያዩ ችግሮችን ለማቃለል ተሠርቷል ብለዋል፡፡

በክልሎች የነበሩ አላስፈላጊ ኬላዎች እንዲቀሩ በማድረግ ኢንዱስትሪዎች ምርቶቻቸውን በቀላሉ ከቦታ ቦታ እንዲያዳርሱ ማድረግ መቻሉን አንስተዋል፡፡

# ዲያስፖራው ከሃምሳ አራት ሚሊዮን ብር በላይ ለፅዱና ለአረንጓዴ ዐሻራ አስተዋፅዖ አድርጓል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ዲያስፖራው ከሃምሳ አራት ሚሊዮን ብር በላይ በማዋጣት በፅዱ እና አረንጓዴ ዐሻራ ተሳትፎ ማድረጉን የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተር አቶ አባይነህ አቅናው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ዲያስፖራው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባደረጉት ጥሪ መሠረት ከሠላሳ ሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ለፅዱ ጎዳና እና አረንጓዴ መርሐ ግብር መዋጮ አድርጓል። ሃያ ሁለት ሚሊዮን ብር የሚገመት ብር ወጪ በማድረግ አስራ አምስት መፀዳጃ ቤቶችን ለመሥራት ቃል ተገብቷል።

የዲያስፖራው በተደራጀ መንገድ ያለውን ክህሎት፣ ዕውቀት እና ቴክኖሎጂ ወደ ሀገሩ በመምጣት አስተዋፅዖ እንዲያደርግ የበኩሉን እንዲወጣ የማሳተፍ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አመልክተዋል። እስከ አሁን ተስፋ ቴክ ኤንድ ሰርቭ ፎር አርቲካል የሚባል የቴክኖሎጂ ካምፓኒ በየጊዜው እየመጣ ሰዎችን በቴክኖሎጂ ዘርፍ ሥልጠና ይሰጣል፤ እንዲሁም ብራይት አፍ ቴክኖሎጂ የሚባል ካምፓኒ በቋሚነት በሚባል ደረጃ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ልምምዶች እየሰጠ እንደሚገኝ አስረድተዋል።



**አቶ አባይነህ አቅናው**

የዲያስፖራው ተሳትፎ ዘርፈ ብዙ ነው ያሉት አቶ አባይነህ፤ በጤናው ዘርፍም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት ሀገሩን እያገለገለ መሆኑን ጠቅሰዋል። እንዲሁም ዕውቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ እየተሳተፈ መሆኑንም ተናግረዋል።

የተለያዩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ የራሱን አስተዋፅዖ እያደረገ መሆኑን በመጥቀስ፤ በዚህ ዓመት ወደ ሰባ ሁለት ቢሊዮን ብር ኢንቨስት በማድረግ ሦስት ሺ ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እና በሌሎች የልማት ፕሮጀክቶች የሚደረገው ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ እና የዲያስፖራው ተሳትፎ በዛው ልክ እየጨመረ መሆኑን የተናገሩት አቶ አባይነህ፣ በግብርና እና በማዕድን ዘርፍ እንዲሁም በቱሪዝም በመደበኛ እየተሳተፉ ያሉ ዲያስፖራዎች እንደሚገኙ አመልክተዋል።

በውጭ ምንዛሪ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ወደ አራት ቢሊዮን ዶላር ገደማ መገኘቱን ጠቅሰው፤ በዚህ ዓመት ከስድስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ማደጉ የዲያስፖራው ተሳትፎ መጨመሩን የሚያመላክት መሆኑን አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የዲያስፖራው ተሳትፎ እንዲጨምር ከተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመሆን በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ትኩረት በማድረግ ያሉ አቅሞችን ከአቅርቦት እና ፍላጎት ጋር በማጣጣም ጥናቶች በማድረግ አገልግሎት ለማዘመን እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

# አረንጓዴ ዐሻራ

## የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ስትራቴጂካዊ ሚና

**ዜና ሐተታ**
**አዲሱ ገረመው**

የአየር ንብረት ለውጥን ለመዋጋትና ቀጣይነት ያለው ልማትን ለማስፋፋት የታለመው የአካባቢ ጥበቃ መርሐ ግብር ዓለም አቀፍ ትኩረትን ከመሳብ ባለፈ የኢትዮጵያን ዓለም አቀፍ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ከፍ ማድረጉ ይጠቀሳል፡፡



**አብዱላኪን ረመዳን፤**

የሀገሪቱን አረንጓዴ ውጥኖች በንቃት የሚደግፉ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች እነዚህ ጥረቶች ኢትዮጵያ ለዓለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ ግቦች ያላትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ኢትዮጵያ በደን መልሶ ማልማትና በታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቶች ግንባር ቀደም በመሆን ለሌሎች ሀገራት አርዓያ በመሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ተፅዕኖ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በማጠናከር ላይ እንደምትገኝም ነው የሚጠቅሱት፡፡

በአሜሪካ ሜኒሶታ ግዛት የሚኖረው ትውልደ ኢትዮጵያዊው አብዱላኪን ረመዳን፤ የአረንጓዴ ዐሻራ ተነሳሽነት በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ዛፎችን በመትከል የአየር ንብረት ለውጥን ለመዋጋት አስተዋፅዖ ማድረጉን ይናገራል፡፡ ይህ ስኬት ኢትዮጵያ የጀመረችውን የነቃ አካሄድ የሚያሳይ እና ለዘላቂነት በሚደረገው የዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ ውስጥ ቁልፍ ተዋናይ ሆና አቋሟን የሚያጠናክር ነው ይላል፡፡



**ወይዘሮ አልፌያ ሸሪፍ**

ዓለም ከአካባቢ ጥበቃ ተግዳሮቶች ጋር እየታገለ ባለበት በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ልማት እያስመዘገበችው ያለው ለውጥ አድናቆትንና ድጋፍን እየሳበ መቀጠሉን፤ ይህም የሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ እያደገ ያለውን ሚና እና ስትራቴጂካዊ ፋይዳ የሚያሳይ እንደሆነ ገልጿል፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ ተከላ መርሐ ግብርን በሚዲያ ከመከታተል ውጪ ተሳትፎ አድርጎ እንደማያውቅና በዘንድሮው ዓመት በአካል ተገኝቶ መሳተፉ ደስታን እንደፈጠረለት የሚናገረው አብዱላኪን፤ ኢትዮጵያ እየተገበረች ባለው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ለዓለም ተምሳሌት መሆን መቻሏንና ይህ በተለይ በዘርፉ ያለውን የዲፕሎማሲ ሥራ እንደሚያጠናክርላት ገልጿል፡፡



**አቶ አቡበከር አሊ፤**

መርሐ ግብሩ በዓለም ላይ እየተስተዋለ ያለውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል ብሎም ለቱሪዝም እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለውም አመላክቷል፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራ ሀገሪቱን በዓለም አቀፍ ደረጃ ይበልጥ እንድትታወቅና ገጽታዋ ከመገንባት አንጻር እየተጫወተ ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ በመጥቀስ፤ ሥራው ሀገር ቤት ያሉትን የሚመለከት ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያንንም ተሳትፎ የሚጠይቅ እንደሆነም ተናግሯል፡፡ ከዚህ አኳያ በተለይ ዲያስፖራው የጀመረውን ተሳትፎ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት፤ ተሳትፎው የፋይናንስ ድጋፍን ጭምር እንደሆነ ጠቅሷል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የዓለም ስጋትና ቀውስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ እየወሰደች ያለው ርምጃ አበረታች እንደሆነ በመግለጽ፤ ካደጉት ሀገራት በላይ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥታ መሥራቷ ለችግሩ መፍትሔ ለመፈለግ ያለትን ቁርጠኝነት ያሳያል ብሏል፡፡

ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ የካናዳ ነዋሪ ወይዘሮ አልፌያ ሸሪፍ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የሀገሪቱን ደን መልሶ የማልማት ቁርጠኝነት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በዚህም ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ምስክር የሆኑ አስደናቂ ውጤቶች እየተመዘገቡ እንዳለም ነው ትዝታቸውን የተናገሩት፡፡

የአየር ንብረት ለውጥን እና በረሃማነትን ለመዋጋት ሰፊ ስትራቴጂ አካል የሆነው ይህ ተነሳሽነት ለሀገሪቱ አዲስ የፈጠራ መንፈስ ማሳያ መሆኑንም ወይዘሮ አልፌያ ገልጸዋል፡፡ ዲያስፖራው ማኅበረሰብም ይህንን ንቅናቄ በመቀላቀል ሰፊ ሥራ መሥራት እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል፡፡

ለሀገር አረንጓዴ ዐሻራ ማኖር በሕይወት ዘመን አንድ ታሪካዊ ክስተት ነው የሚሉት ደግሞ ነዋሪነታቸው በጀርመን ሀገር የሆነው ኢትዮጵያዊ አቶ አቡበከር አሊ ናቸው፡፡ በዚህ ውስጥ ወደ ሀገራቸው በመምጣት መሳተፋቸው ትልቅ ደስታን እንደፈጠረባቸው ገልጸዋል፡፡

በአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ ተከላ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ግንባር ቀደም ሚናዋን እየተወጣች መሆኗን የሚናገሩት አቶ አቡበከር፤ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የተተከሉ ችግኞች ያመጡትን በጎ ተፅዕኖ በዓይን ማየት ይቻላል በማለት፤ በአንድ ወቅት በረሃማ የነበሩ አካባቢዎች ጭምር በደማቅ ችግኞች አጊጠው ቅጠሎቻቸው የፀሐይ ብርሃንን በመሳብ ለአካባቢዎቹ ውበት መፍጠር መቻላቸውን ገልጸዋል፡፡ ከዚህም በላይ ዓለም አቀፍ ፈተና የሆነው የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል የራሳቸው ድርሻ እንዳላቸው አስታውቀዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን ከአካባቢያቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ላይ ጥልቅ ለውጥን ያመጣው የአረንጓዴ ዐሻራ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን ያገኘና የኢትዮጵያንም ሚና ከፍ ያደረገ ስለመሆኑ አቶ አቡበከር ገልጸዋል፡፡

ይህ አካሄድ የአካባቢ ጥበቃን ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ፤ የሀገሪቷን ገጽታ የሚያስተዋውቅ፤ ኢትዮጵያ ተጨማሪ የዲፕሎማሲ ድል እንድትጎናጸፍ የሚያደርግ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ዲያስፖራው አቅሙን አሰባስቦ ሀገር የጀመረችውን የልማት ጉዞ መደገፍ እንዳለበትም አስገንዝበዋል፡፡

# በበጀት ዓመቱ 42 አዋጆች በምክር ቤቱ ፀድቀዋል

## - የዴሞክራሲ ባሕል ለውጥ መታየት መጀመሩን የምክር ቤት አባላት ገልጸዋል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ 42 አዋጆች እና ሁለት መመሪያዎች መፅደቃቸውን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስታወቀ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባዔ ሎሚ በዶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 ዓ.ም በምክር ቤቱ እንዲፀድቁ ከቀረቡ 52 ረቂቅ አዋጆች ውስጥ 42 አዋጆችና ሁለት መመሪያዎች ሕጋዊ ሂደታቸውን ጠብቀው እንዲፀድቁ ተደርጓል፡፡

15 አዋጆች ደግሞ ወደ 2017 በጀት ዓመት መሸጋገራቸውን ጠቁመው፤ ረቂቅ አዋጆች ሕግ ሆነው እንዲወጡ ከ50 በላይ የአስረጂና የሕዝብ ይፋዊ የውይይት መድረኮች በማካሔድ ሕጎቹን ለማዳበር ጠቃሚ ግብዓቶችን የማሰባሰብ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቁመዋል።

የምክር ቤት አባሉ የተከበሩ አቶ ዘካርያስ ኤርኮሌ እንደተናገሩት፤ የተጠናቀቀው በጀት ዓመት በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካው ዘርፍ የተሻለ አፈጻጸም የታየበት፣ በጣም ከፍ ያለ ተሳትፎ የነበረበትና በርካታ ሕጎችን በማፅደቅ የተጠናቀቀ ነበር፡፡

ምክር ቤቱ በሕግ የተሰጡትን ሕግ የማውጣት ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት ሕጎች ለሕዝብ አገልግሎት ጥቅም እንዲሰጡ የሚያስችሉና የክትትል እና የቁጥጥር ሥራንም በተገቢው መልኩ መወጣት መቻሉንም ገልጸዋል፡፡

ምክር ቤቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ምሑራን




እና በመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊነቶች ላይ ሲሠሩ የነበሩ የተለያየ አቅም ያላቸው አባላት የተካተቱበት መሆኑ ለሀገር የሚያስፈልገውንም ሆነ ያሉ እጥረቶችን በአግባቡ ያውቃሉ ብለዋል፡፡

አባላቱ በቀጣይ ዓመት በመንግሥት የሚያዙ በዓመቱ ትኩረት የሚደረግባቸውን የመንግሥት አቅጣጫዎችን በመለየት በስፋት ሊዘጋጁ፣ ተቋማትን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነታቸውንም ለመወጣት በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባም የተከበሩ አቶ ዘካርያስ አሳስበዋል፡፡

የምክር ቤት አባል የተከበሩ ነጃት ግርማ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የምክር ቤት አባላት በነፃነት እንዲጠይቁ፣ የግምገማ እና የሕግ አወጣጥ ሂደቶችም እንዲሻሻሉ እየተደረገ ያለው ተግባር መልካምና የሚበረታታ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የዓመቱ አፈጻጸም አንድ የዴሞክራሲ ባሕል ለውጥ መኖሩን የሚያሳይ ጅምሩ በመሆኑ እየተበረታታ መቀጠል እንዳለበት ጠቁመው፤ የምክር ቤት አባላትና ቋሚ ኮሚቴዎች አስፈጻሚዎችን ባግባቡ መገምገምና መከታተል እንዲችሉ፣ ሕጎች ሲወጡም በጥልቀት ታይተው በስለው እንዲወጡ፣ አባላትም ጥያቄዎችን በነፃነት እንዲጠይቁ በሚያስችል መልኩ ክፍተቶች ታይተው የሚታረሙበትና የሚሻሻሉበት አካሄድ ይበል የሚያሰኝ ነው ብለዋል፡፡

አባላት ድንገት አጀንዳ ተሰጥቷቸው እጅ የሚያወጡና የሚያወርዱ የሚመስላቸው ብዙዎች ናቸው፡፡ ምንም የማይረዱ፣ የተባለውንም የማያውቁ አድርገው ሲነገሩ ስንሰማ እንገረማለን፡፡ ትክክለኛ መረጃ የሌለው ሰው እንደዛ ሊያስብ ይችላል፡፡ ትግበራው ግን እንደዛ አይደለም፡፡ የትኛውም አዋጅ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መድረኮች እንወያይበታለን ሲሉም አክለዋል፡፡

አያይዘው፤ የምክር ቤት አባላት በሀገር ጉዳይም ክርክሮች ያደርጋሉ፡፡ በሠላም፣ በፀጥታ፣ በእድገት እና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውይይቶች ይካሄዳሉ፣ ሃሳብ በማንሸራሸር፣ የመደገፍ የመቃወም፣ በልዩነት የመውጣትም ነፃነት አለን ሲሉ ተናግረዋል።

እኔ የዚህ ዘመን ተመራጭ ነኝ፤ ከእዛ በፊት በነበረው አተገባበር አንድ ሃሳብ አንስቶ ስህተት ከነበረው ተጠርቶ የሚገመገምበት ሂደት ነበረው ያሉት ነጃት(ዶ/ር)፤ አሁን ሃሳብ ማንሳት፣ በነፃነት መናገር ይቻላል፤ ማንም ለምን ይህ ተባለ የሚለው የለም ብለዋል፡፡

# 12 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በክላስተር እርሻ ለመሸፈን ታቅዶ እየተሠራ ነው

**ማሕሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ የምርት ዘመን 12 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በክላስተር በማረስ ከ400 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት ዘርፍ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ኢሳያስ ለማ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ በዘንድሮ የምርት ዘመን እንደ አጠቃላይ ወደ 20 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማረስ የታቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 12 ሚሊዮን መሬት በክላስተር ለማረስና ከ 400 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡

ባለፈው የምርት ዘመን 8 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በክላስተር መታረሱን ያስታወሱት አቶ ኢሳያስ፤ ዘንድሮ በተሻለ የዝግጅት ምዕራፍ በክላስተር የሚታረሰውን መሬትም ሆነ የሚመረተውን ምርት ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ በዚህ ሂደት ላይ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በመሥራት እንዲሁም ደግሞ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ረገድ ሰፊ ሥራዎች መሠራታቸውን አመልክተው፤ ‹‹በተለይም እቅዶች ባለቤት ተሰጥቷቸው እንዲሠሩ በመደረጉ በዚህ ዓመት የተሻለ የክላስተር አፈፃፀም ይኖረናል ብለን እንጠብቃለን›› ብለዋል፡፡

በዚህ ሂደትም ወደ አራት ሚሊዮን አካባቢ ተጨማሪ የክላስተር ቡድኖች ይፈጠራሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቁመው፤ ይህንን ለማሳካት ደግሞ አርሶአደሩን በፈቃደኝነት የማደራጀት እና ሰብሎችን የመምረጥ ሥራዎች መከናወናቸውን አስረድተዋል፡፡

‹‹በዋናነት ደግሞ ዘንድሮ በተለየ መልኩ ክልሎች በራሳቸው አቅደው ያመጡ ከመሆኑ አንፃርም ትልቅ እድገት ነው ተብሎ የሚታሰበው›› ሲሉ የተናገሩት አቶ ኢሳያስ፤ በቂ የሆነ ማዳበሪያ ቀድሞ በማስገባት፣ የዝግጅት ሥራዎች ቀድሞ በማጠናቀቅ ሚኒስቴሩ ከፍተኛ ጥረት ያደረገ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

እንደሥራ አስፈጻሚው ማብራሪያ እንደሃገር የመካናይዜሽን እርሻን ባለፉት ዓመታት ሁለት ሚሊዮን ሄክታር ብቻ የነበረ ሲሆን ዘንድሮ በክረምቱ እርሻ 3 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመካናይዜሽን እንዲታረስ ተደርጓል፡፡ ክረምቱ እስከሚጠናቀቅ እስከ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመካናይዜሽን ለማረስ እየተሠራ ነው፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ በአሁኑ ወቅት ከአንድ ሺ በላይ ትራክተሮች ሃገር ውስጥ የገቡ ሲሆን በክልሎች ድጋፍና ኮላተራል በማስያዝ፡፡ እነዚህ አይነት አገልግሎቶች ክላስተርን ይደግፋሉ፡፡ የዘር አቅርቦታችንም ያድጋል ተብሎ ይታመናል፡፡

አቶ ኢሳያስ፤ መሬትን በመጨመር ሂደት ደግሞ የመስኖ አማራጭን መጠቀም የሚለው ትልቅ ትኩረት የተሰጠው መሆኑንም አስረድተዋል፡፡ በተለይ በመኮሮኒ ስንዴና በዳቦ ስንዴ ላይ ሰፊ ሥራዎች መሠራታቸውን አስታውሰው፤ በአሁኑ ወቅት ከ70 በመቶ በላይ የሚሆነው ስንዴ እርሻ በክላስተር እየታረሰ ነው ብለዋል፡፡

# በዞኑ በ33 ቀበሌዎች ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎች በሌሎች ቦታዎች ለማስፈር እየተሠራ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በዞኑ በ33 ቀበሌዎች ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎች በሌሎች ቦታዎች ለማስፈር የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መሠራታቸውን የቤንች ሸኮ ዞን አስታወቀ። በቅርቡ ባጋጠመው የመሬት ናዳና መሰንጠቅ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ዜጎች ለመደገፍም ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ሥራ መገባቱ ተገልጿል፡፡

የቤንች ሸኮ ዞን ግብርና፣ ደን፣ አካባቢ ጥበቃና ኅብረት ሥራ መምሪያ ኃላፊ አቶ መስፍን ጉብላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በዞኑ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የ33 ቀበሌ ነዋሪዎች በሌሎች ቦታዎች ለማስፈር የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተከናውነዋል።

ከዚህ በፊትም ባጋጠመ መሰል ጉዳት የአንድ ሰው ሕይወት አልፎ እንደነበር አንስተው፤ በሌሎች ላይ ተጨማሪ ጉዳት እንዳያስከትል በተሠራ መልሶ ሰፈራ አንድ መቶ አባወራዎች በጉራ ፈርዳ ወረዳ ማስፈር መቻሉን አመላክተዋል።

በዞኑ ከመጠን በላይ ዝናብ በመጣሉ የተነሳ በሦስት ወረዳዎች ላይ የመሬት ናዳና መሰንጠቅ አደጋ አጋጥሟል ያሉት አቶ መስፍን፤ በዚህም 28 ቤቶች ተደርምሰው ከ241 ሰዎች በላይ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል ብለዋል።

ከሐምሌ 15 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በጉራፈርዳ ወረዳ ኮመታ ሰፈራ እና ነባሩ ኮመታ ቀበሌ እየጣለ ባለው ከባድ ዝናብ ሳቢያ ሦስት ሄክታር የሚሆን ደን በናዳው ምክንያት መውደሙንና የሁለት ሰዎች ሕይወት ማለፉን ገልጸዋል።

በዚሁ ወረዳ የወንዝ ሙላት በአራት ቤቶች ላይ ባደረሰው ጉዳት የሁለት ሕጻናት ሕይወት ማለፉን አቶ መስፍን ተናግረዋል።

በቤንች ሸኮ ዞን የተከሰተው የመሬት መሰንጠቅ እስከ አንድ ሜትር ከ20 የሚሆን ጥልቀት አለው ያሉ ሲሆን በእርሻ ማሳዎች፣ በመንገዶች እንዲሁም በአርሶ አደር ጓሮ ላይ ባሉ የተለያዩ ሰብሎች ላይ ጉዳት ማድረሱንም ነው ያብራሩት።

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ፤ የአደጋው ምልክት ባለባቸው አካባቢዎች ማኅበረሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የግንዛቤ ማስጨበጥ ተግባራት ማከናወን ተችሏል። በተጨማሪም የተፈናቀሉ ዜጎች ባሉበት አካባቢ የተለያዩ የጤና እክሎች እንዳያጋጥሙ የጤና ባለሙያዎች ተመድበው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል።

አሁንም በአንዳንድ ቀበሌዎች የመሬት መሰንጠቅ ምልክቶች የሚታዩ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዞኑ አጠቃላይ የመሬት መሰንጠቅ ጉዳት የደረሰበት ቦታ በርካታ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

እስካሁን 241 የተፈናቀሉ ዜጎች በቀበሌዎች ግቢ፣ በቤተክርስቲያንና ወደ ዘመዶቻቸው የማዘዋወር ሥራ መሠራቱን አስረድተዋል።

እንደ ብሔራዊ ሚትዎሮሎጂ አገልግሎት መረጃ ከሆነ በቀጣይም በቀጣናው ከባድና ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት አሳስበዋል።

በዞኑ ሰሜን ቤንች፣ ሼይ ቤንችና ሚዛን አማን ወረዳዎች በከፍተኛ አደጋ ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን መረጃዎችን ያሳያሉ።

# የምርምር ጥራትን ለማሳደግ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

ሕገወጥ ተግባር ነው።

አንጋፋው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ "የፀረ-ፕላጃሪዝም" ፖሊሲ ከየካቲት 22 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ማድረጉ ይታወቃል። በዚህም ማንኛውም የአንድ ተማሪ መመረቂያ ጽሑፍ በመተግበሪያ ተመርምሮ የሌላ ሰው አለመሆኑ ወይም ከፕላጃሪዝም ነፃ መሆኑ ሳይረጋገጥ ዲግሪ አይሰጠውም፡፡

የሰውን ሥራ የራስ አስመስሎ የማቅረቡ ተግባር በመማር ማስተማሩና በምርምር ሥራ ላይ እያስከተለ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ የፀረ-ፕላጃሪዝም ፖሊሲ በየዓመቱ ተግባራዊ ሆኗል። በዚህም ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሑፍ በሚያዘጋጁበት ጊዜ በጥረትና ልፋታቸው የራሳቸው የሆነ ሥራ ሠርተው እንዲያቀርቡ ያግዛል፡፡

ዩኒቨርሲቲው አሠራሩን በማጠናከር ከሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተሰጠው ውክልና መሠረት፣ የጥናትና ምርምር ጥራትን ለማረጋገጥ የሚረዱ የኤሌክትሮኒክስ መጽሔትና መጻሕፍት (ጆርናሎች) እንዲሁም ለ28 ሺህ ተማሪዎች የሚያገለግል የፕላጃሪዝም ማሳወቂያ መተግበሪያን ለሦስት ዓመታት መጠቀም የሚያስችለውን ፈቃድ መግዛቱን አስታውቋል። አጠቃላይ ወጪያቸውም ከሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዶላር በላይ መሆኑን የአዲስ አበባ የጥናትና ምርምር ዳይሬክተር ታደሰ ፈታሂ (ፕ/ር) ናቸው ያስታወቁት።

የተገዙትን የትምህርት መሣሪያዎች በተመለከተ ዩኒቨርሲቲዎች በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመማር ማስተማር እና የጥናትና ምርምር ሥራን ለማከናወን ዘመኑ የሚጠይቀውን የትምህርት መሣሪያዎች ሊያሟሉ እንደሚገባ የጥናትና ምርምር ዳይሬክተሩ ይናገራሉ።

የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ወጪ ሊያደርጉ የሚገባው ቤተ መጽሐፍት ላይ ነው የሚሉት ፕሮፌሰር ታደሰ፤ በተለይ ለምርምር የሚያግዙ የኢሌክትሮኒክስ መጽሔቶችንና መጻሕፍቶችን ለመምህራንና ለተማሪዎች በማዳረስ ውጤታማ ጥናትና ምርምር እንዲሠሩ ማድረግ የመጀመሪያ ሥራቸው ሊሆን ይገባል ይላሉ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከተለያዩ ከፍተኛ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች በተሰጠው ውክልና መሠረት በርካታ የኤሌክትሮኒክስ መጽሔቶችን፣ መጻሕፍትንና የፕላጃሪዝም ማሳወቂያ መተግበሪያዎችን መግዛቱን ያስረዳሉ።

የተገዛው የኤሌክትሮኒክስ መጽሔትና የፕላጃሪዝም ማሳወቂያ መተግበሪያው የጥናትና ምርምር ጥራትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው በመግለጽ፤ የዩኒቨርሲቲዎቹ መምህራን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ ስለሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተገቢው መልኩ ማወቅና መጠቀም እንደሚገባቸው ያመላክታሉ።

የተገዙት ቴክኖሎጂዎች የዩኒቨርሲቲውን ደረጃ ለማሳደግና ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ለመወዳደር እንዲሁም ተመራማሪዎች ተጨማሪ ግብዓት እንዲያገኙ አጋዥ መሆናቸውን ያነሳሉ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ጄይሉ ዑመር (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማርና የጥናትና ምርምር ሥራውን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ እየሠራ ይገኛል ይላሉ።

የኤሌክትሮኒክስ መጻሕፍትና መጽሔቶቹ የተገዙት በጀርመን፣ በእንግሊዝና በአሜሪካ ከሚገኙ ሰባት አታሚ ድርጅቶች መሆኑን ጠቁመው፤ 16 በኢትዮጵያ የሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንደሚጠቀሙበት ይገልጻሉ። መጻሕፍቱና መጽሔቶቹ ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት አገልግሎት እንደሚሰጡ ይገልጻሉ፡፡

የፕላጃሪዝም ማሳወቂያ መተግበሪያውን ደግሞ አንድ የምረቃ ጽሑፍ የሚያዘጋጅና የምርምር ሥራ የሚሠራ ሰው ሌሎች ሰዎች ከሠሩት የምርምር ሥራ ምን ያህል ገልብጧል ወይም ኮፒ አድርጓል የሚለውን ለመለየት 19 ተቋማት ጥቅም ላይ እንደሚያውሉት ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪ የጥናትና ምርምር መመዘኛ መሣሪያዎችን መኖራቸውን ጠቁመው፤ 14 ተቋማት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውሉት ክትትል ይደረጋል ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ 100 ሺህ የሚሆኑ የኤሌክትሮኒክስ መጻሕፍት፣ አምስት ሺህ የሚደርሱ የትምህርት መጽሔቶች (ጆርናሎች) መገዛታቸውንና እያንዳንዳቸው በውስጣቸው የተለያዩ ጥናታዊ አርቲክሎች መያዛቸውን ነው ያስታወቁት። የፕላጃሪዝም ማሳወቂያ መተግበሪያው ደግሞ የ28 ሺህ ተማሪዎችን ጥናታዊ ጽሑፎች ለመፈተሽ እንደሚረዳ ይገልጻሉ፡፡

የትምህርትና የጥናትና ምርምር ጥራትን ለማሳደግ እነዚህ የትምህርት መሣሪያዎች ወሳኝ ናቸው የሚሉት ጄይሉ(ዶ/ር)፤ የትም ሀገር ያልተሠራ አዲስ ጥናትና ምርምር ለመሥራት የፕላጃሪዝም ማሳወቂያ መተግበሪያው ወሳኝ በመሆኑ ሁሉም የትምህርት ተቋማት ሊጠቀሙበት ይገባል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

በከፍተኛ ወጪ የተገዙትን የኤሌክትሮኒክስ መጻሕፍቶችና የፕላጃሪዝም ማሽን በአግባቡ ማወቅና መጠቀም ይገባል የሚሉት ጄይሉ (ዶ/ር)፤ የተገዙትን የትምህርት መሣሪያዎች በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ከተቻለ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅምን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክት ይገልጻሉ፡፡

ለዩኒቨርሲቲዎች የምርምር መጽሔትን በቴክኖሎጂ አስደግፎ ማቅረብ፣ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት ውጤታማ ጽሑፍ እንዲያዘጋጁና ተመራማሪዎችም አስፈላጊውን የምርምር ጽሑፍ እንዲያገኙ ዩኒቨርሲቲው ያከናወነው ተግባር ይበል የሚያሰኝ መሆኑ የዩኒቨርሲቲው ምሑራን ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ አፈጻጸም ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ!

የኢንቨስትመንት ዘርፍ በአጠቃላይ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በባሕሪው ሠላምና ፀጥታን በእጅጉ ይፈልጋል፤ ለኮሽታም ሳይቀር ስስ እንደሆነ ይነገርለታል። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ በሀገሪቱ የተለያዩ ግጭቶች ተከስተውም፣ የሰሜን ኢትዮጵያን ያህል ግዙፍ ጦርነት ተካሂዶም፣ ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ በሀገሪቱ ላይ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ያደጉት ሀገሮች ጫናዎች አሳድረውም፣ ኮቪድ አሉታዊ ተፅዕኖውን አሳርፈውም ከመቀዛቀዝ ያለፈ፣ ስር የሰደደ ችግር አልታየበትም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግም በሀገሪቱ መነቃቃት እየታየባቸው ከሚገኙ ዘርፎች መካከል ይሄው የኢንቨስትመንት ዘርፉ ይጠቀሳል።

መቀዛቀዙም ቢሆን ችግሮቹ መወገዳቸውን ተከትሎ ወደ መሟሟቅ ተሸጋግሯል። በሌሎች ሀገሮች ባልተለመደ ሁኔታ እነዚህ ችግሮች በሀገሪቱ ቢከሰቱም የውጭዎቹን ጨምሮ በርካታ ባለሀብቶች በዘርፉ ሲሰማሩበት ቆይተዋል። በሀገሪቱ የታዩት ችግሮች በሌሎች ሀገሮች እንደሚታዩት ችግሮች አይነት እንዳይደሉና ሊፈቱ እንደሚችሉም በማመን ነበር በባለሀብቶቹ በኢንቨስትመንቱ መስክ ሲሠማሩ የነበሩት።

የኮቪድ ወረርሽኝ እየቀነሰ ሲመጣና የሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት በፕሪቶሪያው ስምምነት መሠረት ሲያቆም ደግሞ ዘርፉ ፈጥኖ ያገገመበት ሁኔታ ታይቷል። ይህ መነቃቃት በተጠናቀቀው 2016 በጀት ዓመትም ታይቷል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የ2016 በጀት ዓመትን አፈጻጸም በቅርቡ ባስታወቀበት ወቅት እንደጠቆመውም በኢንቨስትመንት ዘርፉ ላይ ጫና አሳድረው የነበሩ ችግሮች ደረጃ በደረጃ መፍትሔ እያገኙ በመምጣታቸው በዘርፉ መነቃቃት እየታየ መጥቷል። በበጀት ዓመት በብዙ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ተስፋ ሰጭ ውጤት የተመዘገበበት ሁኔታም ይህንኑ እንደሚያመለክት ተጠቁሟል።

በዘርፉ ለውጦች ከታየባቸው መካከልም የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ይጠቀሳል። በኢንቨስትመንት ዘርፉ ፈቃድ ከወሰዱ ባለሃብቶች መካከል ከ75 በመቶ በላይ የሚሆኑት በማምረቻው ዘርፍ የሚሰማሩ ናቸው። ባለሀብቶች ሊሠማሩባቸው የሚችሉ በርካታ የኢንቨስትመንት ዘርፎች እንደመኖራቸውና የተሳተፉበት ሁኔታም ቢኖርም አምራች ዘርፉ ብልጫውን ይዞ መገኘት ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ደረጃ ብልጫውን ይዞ መገኘቱ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ጥሩ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ያስገነዝባል።

እንደሚታወቀው ሀገሪቱ ባለሀብቶች በአምራች ዘርፉ እንዲሰማሩ ለማድረግ በትኩረት መሥራት ከጀመረች ቆይታለች። ለሀገር በእጅጉ የሚበጀው የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ መሆኑ በእጅጉ ታምኖበት በሰፊው ጥረት ተደርጓል፤ የማምረቻ ቦታ እና የመሠረተ ልማት ችግርን ለመፍታት ሲባልም የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በብዛት በመገንባት ለባለሀብቶች በማቅረብ ላይም ተሠርቷል። ከግብርናው ወደ ኢንዱስትሪው የሚደረገውን ሽግግር ለማፋጠን ለዚህ ዘርፍ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ ታምኖበት ወደ ዘርፉ ለሚገቡ የውጭም ሆኑ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የማበረታቻዎች ተደርገዋል፤ እየተደረጉም ናቸው።

ዘርፉ ሥራ ከጀመረ በርካታ ዓመታት ቢቆጠሩም፣ ቆይቶም ቢሆን በዘርፉ ለውጦች መመዝገብ ጀመረዋል። ያለፈው በጀት አፈጻጸም ከሌሎች ኢንቨስትመንቶች አኳያ ሲታይ የታየበት ሰፊ ለውጥ በተዓምር የመጣ አይደለም፤ በግብርናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን በማምጣት ኢንዱስትሪው የግብርናውን ስፍራ እንዲይዝ ለማድረግ፣ በተለይ ከለውጡ ወዲህ ደግሞ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እየወጣባቸው ከውጪ የሚመጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የተከናወኑ ጠንካራ ሥራዎችን ተከትሎ የመጣ ውጤት ነው።

ባለፉት የለውጡ ዓመታት ባለሀብቶች ወደ አምራች ኢንዱስትሪው በስፋት እንዲገቡ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፤ የኢንቨስትመንት አዋጁ ተሻሽሏል፤ ሀገሪቱን ኢንቨስትመንት በቀላሉ የምትስብ እንድትሆን ለማድረግ ተሠርቷል፤ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለውጭ ባለሀብቶች ብቻ ይቀርቡ የነበረበትን ሁኔታ በማሻሻል በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፓርኮቹን ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ጭምር ክፍት የማድረግ ሥራዎች ተከናውነዋል፤ ወደ ፓርኩ ለመግባት የሚያስፈልጉ ክፍያዎችን በኢትዮጵያ ገንዘብ መፈጸም እንዲቻል ተደርጓል፤ ይህን ሁሉ ተከትሎም ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ እየተሳቡ ያገኛሉ። እነዚህና የመሳሰሉት ተግባሮች የአምራች ዘርፉ አፈጻጸም ከሌሎች ዘርፎች አፈጻጸም የተሻለ እንዲሆን አርገዋል ብሎ መውሰድም ይቻላል።

በተለይ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ እየተከናወነ ባለው ተግባር የዘርፉ ተግዳሮቶች የሆኑትን የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ የቦታ፣ የገበያና የመሳሰሉትን ችግሮች ለመፍታት የተከናወኑ ተግባራትም ለዚህ ውጤት የራሳቸው ድርሻ አላቸው። በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች ሌሎች ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ እንዲሳቡ አላደረገም ማለትም አይቻልም።

በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ እየታየ ያለው ለውጥ የሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ልማት በጥሩ ጉዞ ላይ መሆኑንም ያሳያል። በዘርፉ እየታየ ያለው ለውጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢንቨስትመንቱን ሊፈትኑ የሚችሉ ችግሮች ዛሬም ጥቂት ባልሆኑበት ሁኔታ፣ እንደ ሀገርም ቢሆን የዘርፉ ገበያ የሆነው አሜሪካ ከሰሐራ በታች የሚገኙ ሀገሮች ምርቶቻቸውን ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገሪቱ እንዲያስገቡ የፈቀደችው ዕድል /አጎአ/ ለኢትዮጵያ ዝግ በሆነበት፣ አልፎ አልፎ የፀጥታ ችግሮች አሁንም በሚታዩበት ሁኔታ ዘርፉ በለውጥ ላይ መገኘቱ ኢንቨስትመንቱ በጥሩ መሠረት ላይ የቆመና በቀላሉ የማይደነግጥ መሆኑን መሆኑን ያመለክታል።

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በቀጣይም በአፈጻጸሙ ለውጥ ሊያስመዘግብ እንደሚችል ባለፈው በጀት ዓመት የተከናወኑት ተግበራት ለቀጣዩ ሥራ ጥሩ መሠረት ሊሆኑ እንደሚችሉ መልካም ማሳያዎች አሉ። ይህን አቅም፣ በዘርፉ የተገኙ ልምዶችን በመቀመር የተገኘውን ውጤት ከመጠበቅ ባሻገር የላቀ እንዲሆን ለማድረግ አሁንም ጠንክሮ መሥራት ይገባል። የአምራች ዘርፉን ከሚጠበቅበት ስፍራ ማድረስም ይህንኑ ይፈልጋል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የ5ሚሊዮን ኮደሮች ሥልጠናና ሀገራዊ ፋይዳው

ክብረአብ

ቴክኖሎጂና አዲስ የፈጠራ ሥራ የሰው ልጆችን ሕይወት በብዙ አሻሽሏል፡፡ ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከግብርና እና ከሌሎች ዘርፎች አንፃርም የሚሰጠውን ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ላሉና በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት ደግሞ የቴክኖሎጂ ፋይዳ ከምንለው በላይ ትልቅ ነው።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የማደግ ዕድል እንዳላት ሀገር ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን ጥረት እያደረገች ትገኛለች። በሁሉም መስክ ማለትም የማኅበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል፣ ዘመናዊ ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ ግብርናን ዘመናዊ በማድረግ በምግብ እራስን ለመቻል፣ ለጤና ብሎም ለወታደራዊ አገልግሎት፣ በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን በቴክኖሎጂ መታገዝ የግድ ሆኗል።

በቅርቡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አምስት ሚሊዮን ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርገውን የኢትዮጵያ ኮደሮች ኢንሼቲቭ አስጀምረዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሳይንስ ሙዚየም ኢንሼቲቩን ባስጀመሩበት ወቅት እንደተናገሩት ኢንሼቲቩ ሠልጣኞችን ዘመኑን በዋጀው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሚያደርግ ይሆናል። የኢትዮጵያ የነገ ተስፋዎች የሆኑ ወጣቶችም ሥልጠናውን በጥሞና በመከታተል ሥራ ፈጣሪ፣ ኩባንያ ፈጣሪና በዓለም ገበያ ተወዳድረው የሚቀጠሩ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም ይህንን ትልቅ ዕድል በአግባቡ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የዲጂታል ክህሎት በዲጂታል የታገዘ ማኅበረሰብ ለመፍጠር፣ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠርና ለመሰማራት ወሳኝ እየሆነ መጥቷል። ነገር ግን ኢትዮጵያ በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ጋር ካሉ አገራት ጭምር ስትወዳደር በዲጂታል ክህሎት ወደ ኋላ ቀርታለች። አዲሱ ትውልድ ተገቢው የዲጂታል ክህሎት ከሌለው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን ካለመቻሉ ባሻገር እንደ ሀገርም እድገትን የሚጎዳ ነው።

በመሆኑም ኢትዮጵያ በዲጂታል ክህሎት ያለባትን ክፍተት ለመሙላት የመሠረታዊ ኮምፒውተር እውቀትና ሁለንተናዊ የዲጂታል ክህሎት መርሐ ግብር ተዘጋጅቶ ለወጣቶች ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ የአምስት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ኮደርስ ፕሮግራምም የኢትዮጵያ ወጣቶች ተገቢውን የዲጂታል ክህሎት እንዲኖራቸው ለማድረግ የተቀረጸ በመሆኑ ፋይዳው ከፍተኛ ነው።

አምስት ሚሊዮን የኢትዮጵያ "ኮደርስ" ፕሮግራም በኢትዮጵያ እና በተባበሩት ዓረብ ኢምሬትስ መንግሥታት መካከል በተደረገ ስምምነት የተነደፈ የዲጂታል ክህሎት ሥልጠና መርሐ ግብር ነው። የመርሐ ግብሩ ዓላማ ወጣቱ ትውልድ በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ መሳተፍ የሚያስችለውን የዲጂታል ክህሎት እንዲኖረው ማስቻል ነው።

መርሐ ግብሩ ለሁሉም ተደራሽ የሆኑ የኦንላይን ኮርሶችንና ሌሎች ደጋፊ የሆኑ አገልግሎቶችን በማቅረብ እ.ኤ.አ በ2026 አምስት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን በፕሮግራሚንግ፣ በዳታ ሳይንስ እና አንድሮይድ ልማት መሠረታዊ የዲጂታል ክህሎት ማስታጠቅን ግብ ያደረገም ነው።

ዘመኑ ቴክኖሎጂ የሥራ መሣሪያ ብቻ ሳይሆን የለውጥ አራማጅ የሆነበት ምዕራፍ ላይ ደርሷል። የሀገራችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ በወጣቶች እጅ እንደሚሆንም ይታወቃል። የነገዋን ኢትዮጵያ የሚቀርፁት የፈጠራ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች እነዚህ ወጣቶች ናቸው። በመሆኑም የኢትዮ ኮደርስ ፕሮግራም ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን በዲጂታል ሥነ ምሕዳሩ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያስችላቸውን ክህሎትና እውቀት በማስታጠቅ አዳዲስ ዕድሎች እንዲፈጠርላቸው እና ሀገራችን በቴክኖሎጂው መስክ ወደፊት እንድትገሰግስ በር የሚከፍት ነው የሚል እምነት አለኝ።

የኢትዮ ኮደርስ ፕሮግራም ወጣቶችን ለማብቃት፣ ፈጠራን ለማጎልበት እና የዲጂታል ዘመንን ግዙፍ አቅም ለመጠቀም እንደ ሀገር ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ በመሆኑ የተጀመረው ኢንሼቲቭ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ ሊሆን ይገባል እላለሁ።

እንደ ሀገር ምንም ያህል መሠረተ ልማት ቢገነባ፣ መተግበሪያዎች ቢለሙ፣ የሕግ ማዕቀፎች ቢረቀቁ፤ የተገነቡ መሠረተ ልማቶች ላይ ተመሥርተው የሚለሙ አፕሊኬሽኖችን የሚጠቀም ሰው ካልተፈጠረ የለሙትን መሠረተ ልማቶች ተጠቅሞ ያለውን ሃሳብ ወደ መተግበሪያ ለውጦ አገልግሎቶችን የሚያለማ የሰው ኃይል ከሌለን የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እቅዱ በታለመለት ልክ ግቡን ሊመታ አይችልም።

ስለሆነም የዲጂታል ትራንስፎርሜሽኑን ለማስፋትና ለማስቀጠል የዲጂታል ዕውቀት እና ክህሎት ያለው በርካታ የሰው ኃይል ማዘጋጀትና ማብቃት የግድ ይለናል። በዚህ ረገድ ባለፉት የዲጂታል ስትራቴጂው ዓመታት ጥረቶች የነበሩ ቢሆንም በዘመቻ መልክ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚያካትቱ የዲጂታል ክህሎት ፕሮግራሞች ተቀርጸው በስፋት አልተተገበሩም።

ይህም አካታች የዲጂታል ኢኮኖሚ ልማት እውን ከማድረግና የትራንስፎርሜሽኑን ቀጣይነት ከማረጋገጥ አንጻር ትልቅ ተፅዕኖ ያለው ጉዳይ ሆኗል። ለዚህም የአምስት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ኮደሮች ኢኒሼቲቭ የወጣቶችን የዲጂታል ክህሎት በማሳደግ ረገድ አንዱ ምላሽ ሆኖ መምጣቱ ይባል የሚያሰኝ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ቴክኖሎጂ በትምህርት መቶ ሚሊዮን ሕዝብ ማስተማር እንዲሁም በጤናው ዘርፍ ቁጥሩ ከፍተኛ ለሆነ ሕዝብ ሕክምና ተደራሽ ማድረግ አይቻልም። በግብርናውም በቴክኖሎጂ ተጠቅመን ካልሠራን በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ መመገብ አይታሰብም፡፡ ትልቅ ቁጥር ያለው ሕዝብ ነው ያለውና ወደ እያንዳንዱ ቤት መድረስ የሚቻለው በቴክኖሎጂ ነው፡፡ ስለዚህ ከምንም በላይ እንደ ሀገር ለዘርፉ ትኩረት መስጠት የውዴታ ግዴታ ነው ብዬ አስባለሁ።

ቴክኖሎጂ በጥቂት የሰው ኃይልና ቦታ ትላልቅ ሥራዎች ለመሥራት ምቹ መሆኑ ዘርፉን በብዙ ተመራጭ እንደሚያደርገው እሙን ነው። በሚመጣው ዘመን ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ለቴክኖሎጂ ሥራና ምርምር ትልቅ ትኩረት ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ መንግሥት የነቃ ተሳትፎ በማድረግ በዘርፉ ለተሰማሩ ግለሰቦችና ተቋማት አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉ የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ መሥራት አለበት እላለሁ።

ያደጉትም ሆነ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ቴክኖሎጂን በሚያስፈልጋቸው ዘርፎች እንደ አስፈላጊነቱ እየተጠቀሙበት ችግሮቻቸውን እየፈቱ ይገኛሉ። ኢትዮጵያም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለቴክኖሎጂ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ትገኛለች። ቴክኖሎጂን በመጠቀም የግብርና፣ የጤና፣ የደኅንነት፣ እና መሰል ዘርፎችን አቅም ለማሳደግ እየተሠራ ይገኛል።

የተለያዩ ዓውደርዕዮች በማዘጋጀት በዘርፉ የተሰማሩ ግለሰቦች የቴክኖሎጂ ፈጠራ ሥራዎችን ማሳየት እንዲችሉ ዕድል መፍጠር ይስተዋላል ይህ የሚበረታታና ይበል የሚያሰኝ ነው። ነገር ግን በዘርፉ ዓለም ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንፃር አሁንም እንደ ሀገር ያለንበት ደረጃ ዝቅተኛ በመሆኑ አሁን ከተሰጠው በላይ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ይገባል።

# በጋምቤላ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር መላኩ ወልደማሪያም መድረኩን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ፤ ኮሚሽኑ ያዘጋጀው የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ በክልሉ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ሀገራዊ መግባባት ሊደረግባቸው ያስፈልጋል የሚሏቸውን መሠረታዊ ጉዳዮች የሚያቀርቡበት ነው።

ኢትዮጵያ መሠረታዊና ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጎልተው የሚታዩ የሀሳብ ልዩነቶችና አለመግባባቶች የሚስተዋሉባት ሀገር ነች ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ላለመግባባቶቹ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ከምንጫቸው በሐቅና በእውነት በመለየት፣ አጀንዳ ቀርጾ ምክክር በማድረግ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል ብለዋል። መግባባት ላይ የተደረሰባቸውንም ጉዳዮች ተግባራዊ በማድረግ አዲስ ታሪክ የምንጽፍበት ሂደት ላይ እንገኛለን ሲሉ አክለው ተናግረዋል።

በእስካሁኑ ሂደትም አዲስ አበባንና ድሬዳዋ ከተሞችን ጨምሮ በ10 የኢትዮጵያ ክልሎች ተሳታፊዎችን መለየታቸውን አስታውሰው፤ በመዲናዋ የአጀንዳ ልየታ የምክክር ምዕራፍ መካሄዱን እንዲሁም ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማኅበረሰብ ክፍሎች ተወካዮችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር አጀንዳ የሚሰበሰብበት ተመሳሳይ መድረክ እያካሄደ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ኮሚሽኑ ከዚህ ቀደም በጋምቤላ ክልል በየወረዳው ከሚገኙ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት የሚሳተፉ ተወካዮችን አስመርጦ ማዘጋጀቱን አንስተው፤ ከዛሬ ጀምሮ ለሰባት ተከታታይ ቀናት በክልሉ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ እንደሚካሄድ አመላክተዋል።

በመሆኑም ኮሚሽኑ በሚያከናወነው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ላይ የክልሉን የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ ተሳታፊዎችና በክልሉ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች እንደሚገኙ ጠቁመው፤ በተጨማሪ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሲቪክ ማኅበራትና የመንግሥት አካላት፣ የተለያዩ ተቋማትና ማኅበራት ተወካዮች እንዲሁም ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች የሚመካከሩበት እና የአጀንዳ ሀሳቦቻቸውን የሚያዘጋጁበት ሂደት እንደሚፈጠር ተናግረዋል።

በአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፉ ከአንድ ሺህ 300 በላይ ተወካዮችን ተሳታፊ መሆናቸው ኮሚሽነሩ ገልፀዋል።

መላው የጋምቤላ ክልል ነዋሪ የምክክር እና የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱን ፋይዳ በመረዳት ዝግጅት እንዲያደርግና በንቃት በመሳተፍ ለሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ስኬት የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ስም ጥሪ አቅርበዋል።

# ኢትዮጵያ ወደ ተሚሳ የማክሮ ኢኮኖሚ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

በመግለጫው ተጠቁሟል።

ከ2010 እስከ 2015 ባሉት በጀት ዓመታት በአማካይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ሰባት ነጥብ አንድ በመቶ ደርሷል።

በዚህም ሀገራችን በአፍሪካ ኢኮኖሚ ምሕዳር ጉልህ ሚና ያላት ሀገር ለመሆን በቅታለች።

በመግለጫው መሠረት፤ ኢትዮጵያ ከሰሐራ በታች ካሉ አፍሪካ ሀገራት የሦስተኛው ትልቁ ኢኮኖሚ ባለቤትም ሆናለች። መንግሥት የግብር ገቢ የመሰብሰብ አቅሙ ተሻሽሏል። በቅርቡ የፀደቀው ሁለተኛው ምዕራፍ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ቀሪ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ መንግሥት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያረጋግጥ ነው።

ፕሮግራሙ በሚተገበርበት ወቅት ከፍተኛ እና የተረጋጋ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ነጠላ አኀዝ የዋጋ ግሽበት ይኖራል ተብሎ ግብ መጣሉ ተመላክቷል። የውጭ ምንዛሪ መዛባትን በማስተካከል፣ የፋይናንስ ዘርፉን ይበልጥ በማጠናከር፣ የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር፣ የታክስ ገቢን በማሳደግ፣ የመንግሥትን ኢንቨስትመንት ውጤማነት በማሻሻል፣ የመንግሥት ዕዳ ዘላቂነትን በማረጋገጥ፣ የባንክ ዘርፍን ተወዳዳሪነትና ጤናማነት በማጎልበት እና የንግድና ኢንቨስትመንት ከባቢን በማሻሻል፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዘመናዊና ተወዳዳሪ የኢኮኖሚ ሥርዓትን ለመገንባት ሰፊ ሀገራዊ ግብ መቀመጡ ተብራርቷል።

ባለፉት ዓመታት፣ ለሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራማችን ትግበራ ከፍተኛ የፋይናንስ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ጥረቶችና ድርድሮች ሲደረጉ መቆየታቸው ተገልጿል።

ድርድሮቹ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቁና የዜጎቻችንን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ መሆኑን ለማረጋገጥ በዕውቀትና በብስለት እንዲመሩ መደረጋቸው ተጠቁሟል። በዚህም መንግሥት ባስቀመጣቸው ዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ ዓላማዎችና የፖሊሲ ማሻሻያዎች ቅደም ተከተል መሠረት ስምምነት ላይ ለመድረስ ተችሏል ሲል ጽሕፈት ቤቱ አስታውቋል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት፣ በዓለም ባንክ እና በሌሎች ወሳኝ የልማት አጋሮቻችን የሚደገፍ ነው።

የተመሠረተውም በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራማችን እና በመካከለኛው ዘመን የኢንቨስትመንትና የልማት እቅዳችን ላይ ነው።

በመግለጫው መሠረት፤ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ቁልፍ ዓላማዎችና ግቦች መካከል የውጭ ምንዛሪ መዛባትን ማስተካከልና የረጅም ጊዜ የውጭ ክፍያ ሚዛን ጉድለት ችግሮችን መፍታት አንዱ ነው። የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፉን በማዘመን የዋጋ ንረትን መቀነስና የዕዳ ተጋላጭነትን በመፍታት፣ የሀገር ውስጥ ገቢን በማሳደግና ሀገራዊ የልማት ፍላጎቶቻችንን በሀገር ውስጥ አቅም ለማሳካት ምቹ መደላድል መፍጠር ሌሎቹ ግቦች ናቸው።

በተጨማሪ የፋይናንስ ዘርፉን አካታችነት፣ ተወዳዳሪነትና ጤናማነት ማጠናከር እንዲሁም የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል፣ የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋም እና የምግብ ሉዓላዊነትን በማረጋገጥ፤ ጠንካራ፣ አካታች እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ሥርዓትን መገንባት ግቦቹ መሆናቸው ተመላክቷል።

ከፖሊሲ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ጋር ተያይዘው የሚመጡት አዳዲስ የልማት ፋይናንስ፣ የንግድና የኢንቨስትመንት ዕድሎችን በአግባቡ እንድትጠቀም ያስችላታል። እንዲህ ያለ የትብብር አጋርነትና ቅንጅት ሀገራዊ የግሉ ዘርፍ የሚመራው የዕድገት አቅጣጫ እንዲሳካ ለማድረግ ለግሉ ዘርፍ መጠነ ሰፊ ዕድሎችን ይፈጥራል ሲል ጽሕፈት ቤቱ አስታውቋል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎቹ ዋና ዋና ርምጃዎችና የሚጠበቁ ሀገራዊ ፋይዳዎችን በተመለከተ፣ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት፣ በዓለም ባንክና በሌሎች ወሳኝ የልማት አጋሮቻችን የሚደገፈው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራማችን ለሀገራችን ኢኮኖሚ በርካታ ጥቅሞችን እና ውጤቶችን እንደሚያስገኝ ይጠበቃል።

ከማሻሻያው ከሚወሰዱ ርምጃዎች መካከል በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት በተለይ የውጭ ምንዛሪ ግብይት በገበያው አማካኝነት እንዲበየን የማድረግ ሂደት አንዱ ነው።

ሌላኛው ቁልፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ የማሻሻያ ርምጃ የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፉን ማዘመን ነው። የሦስት ዓመት የብሔራዊ ባንክ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝቅተኛ እና የተረጋጋ የዋጋ ንረት መኖሩን ማረጋገጥ እንደመሆኑ መጠን፣ ባንኩ ከንግድ ባንኮች ጋር በሚያደርገው የንግድ ግብይት በወለድ ተመን ላይ የተመሠረተ የገንዘብ ፖሊሲ ሥርዓት እንዲፈጠር ቅድሚያ ይሰጣል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይህንን የፖሊሲ ማሻሻያ ትግበራ ጀምሯል። በተጨማሪም የፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያችን የመንግሥት ፋይናንስ ጫናዎችን እንዲቀንሱ ያደርጋል። ውጤቶቹም ትክክለኛ የፖሊሲ መስተጋብር በመፍጠር ማክሮ ኢኮኖሚው እንዲረጋጋ ያደርገዋል።

የፖሊሲ ርምጃዎቹ ከአጠቃላይ ሀገራዊ የረጅምና የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶቻችን ጋር ተጣጥመው ይከናወናሉ። እንዲሁም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅ እና የዜጎቻችንን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲተገበሩ መንግሥት ከፍተኛ የክትትልና የድጋፍ ማዕቀፎችን እንደሚዘረጉ ተጠቁሟል።

ለዚህም በሁሉም በሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እና በመንግሥታዊ ተቋማት በኩል አስፈላጊ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል። በሁሉም በሚመለከታቸው ተቋማት በኩል የፖሊሲ ትግበራ አፈጻጸም ወጥነት እንዲኖር መንግሥት ጠንካራ የፖሊሲ ማሻሻያ አመራር መኖሩን ያረጋግጣል ብሏል ጽሕፈት ቤቱ።

ፕሮግራሞች ድጎማ ይደረግላቸዋል። ለዝቅተኛ ደመወዝ ተከፋይ የመንግሥት ሠራተኞች የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎቹ ሊያስከትሉ ከሚችሉት የአጭር ጊዜ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመጠበቅ አስፈላጊ የደመወዝ ድጎማና ማሻሻያዎች ለተወሰኑ ጊዜያት ይደረጋሉ ሲል በመግለጫው አመላክቷል።

የነዳጅ ዋጋ ጭማሪውን መንግሥት በከፊል እንደሚደጉምና የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ሂደት ቀጣይነት ያለው ግምገማ እንደሚደረግበት ተጠቁሞ፤ መንግሥት በወቅታዊ መረጃ ላይ በመመሥረት በፕሮግራሙ ላይ ወቅታዊ፣ አስፈላጊ እና ተገማች የፖሊሲ ማስተካከያዎችን እንደሚያደርግ አስታውቋል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት እንደገለጸው፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርሙን በተመለከተ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች በገንዘብ ሚኒስቴርና በብሔራዊ ባንክ በኩል በየጊዜው ይፋ ይደረጋል።

# የሆርቲካልቸር ማነቆዎችና ምርታማነቱን...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

ግብርና ሚኒስቴርም በዘርፉ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍና ለኢኮኖሚው የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ ለማሳደግ የሚያስችል ብሔራዊ ስትራቴጂ አዘጋጅቷል:: ስትራቴጂው በ10 ዓመታት ውስጥ የሚተገበር ይሆናል:: በየዓመቱ የሚያስገኘውን የውጪ ምንዛሪ ወደ 3 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዶላር፣ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድልም ወደ 2 ሚሊዮን ማሳደግ በስትራቴጂው ከተቀመጡ እቅዶች መካከል ይጠቀሳሉ::

ለመሆኑ በዘርፉ የሚስተዋሉ አንኳር ችግሮች ምንድን ናቸው? ስትራቴጂውስ እነዚህን ተግዳሮቶች በመቅረፍ በኩል ምን ሚና ይኖረዋል?

የፍሪ-ኤል ኢትዮጵያ እርሻና ማቀነባበሪያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ የቢዝነስ ኦፕሬሽን ማናጀር አቶ ፋሲካ ሥዩም እንደሚናገሩት፤ በዘርፉ የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ የፀጥታ መደፍረስ፣ መሠረተ ልማት አለመሟላት፣ አንዳንድ ክልሎች ላይ የሚጠየቅ የኮቴ ክፍያ ለሥራው እንቅፋት ፈጥሯል::

አንድ ሄክታር ለማልማት አራት ሰው ይፈልጋል የሚሉት አቶ ፋሲካ፤ አምስት ሺህ ሄክታር የምናለማ ከሆነ 20 ሺህ ሰው ያስፈልጋል ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ጋር ተቀናጅቶ ለመሥራት እየሞከረ ነው:: ይሁን እንጂ ችግሩ በሚፈለገው ልክ መፍትሔ ባለማግኘቱ ሙያተኞችን ከውጭ ሀገራት እየመጡ እንደሚሠሩ ያስረዳሉ።

በደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ በሚገኙ እርሻዎች ላይ ለአብነት የኤሌክትክ ኃይል ባለመኖሩ የጄኔሬተርና ሶላር ፓኔሎችን ነው ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙት:: ጀኔሬተሩ፣ መኪኖች፣ ነዳጅና ሌሎችም ለሥራ የሚውል ማሽኖች ነዳጅ ይጠቀማሉ:: ለዚህም በወር እስከ 100 ሺህ ሊትር ነዳጅ ይጠይቃል፤ ነገር ግን እንደአምራቾች የተፈቀደልን እስከ 50 ሺህ ሊትር ብቻ ነው:: ወጪውም ከፍተኛ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

ኤሌክትሪክ በሌለበት ቦታ ላይ የኤሌክትሪክ መኪኖችንና ማሽኖችን እንዲገቡ ግፊት ይደረጋል። ቀደም ሲል ያዘዟቸውን በነዳጅ የሚሠሩ መኪኖች ማሽነሪዎች አምራቾች ማስገባት ባለመቻላቸው ጂቡቲ ወደብ ላይ የኮንቴነር ኪራይ ይከፍላሉ:: ስለሆነም መንግሥት ፖሊሲውን ድጋሚ ገምግሞ ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የነዳጅ መኪኖችን ማስገባት ቢፈቅድ ካልሆነም አካባቢው ላይ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት በበቂ ሁኔታ ቢያዳርስ ዘርፉን ማነቃቃት ይቻላል ይላሉ።

ችግሮች የሚቀረፉ ከሆነ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት የወሰድነውን 10 ሺህ ሄክታር መሬት ሙሉ በሙሉ አልምተን ተጨማሪ 20 ሺህ ሄክታር መሬት ወስዶ ለማልማት እቅድ ይዘናል። ሌሎችም አምራቾች በተመሳሳይ አቅማቸውን ማሳደግና በምግብ ራስን ለመቻል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፣ የውጪ ምንዛሪ ገቢን መጨመርና በርካታ የሥራ ዕድል መፍጠር ይቻላል ሲሉ ያብራራሉ።

ስትራቴጂው በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ትልቅ አቅም ይሆናል ያሉት አቶ ፋሲካ፤ ስትራቴጂውን በአፋጣኝ ወደ ሥራ እንዲገባና በዘርፉ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች እንዲቀረፉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በትብብር መሥራት እንዳለባቸው ይጠቁማሉ::

የኢትዮጵያ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራችና ላኪዎች ማኅበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ዘውዴ በበኩላቸው፤ የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት፣ የፀጥታ መደፍረስ እና ሌሎችም ችግሮች የሆርቲካልቸር ዘርፉ በሚፈለገው ደረጃ ኢኮኖሚውን እንዳይደግፍ አድርጓል ይላሉ::

ባለፉት ዓመታት 10 የሚደርሱ ኩባንያዎች ችግር እንደገጠማቸው የሚያስታውሱት ዳይሬክተሩ፤ በአማራ ክልል ከተፈጠረው የፀጥታ ችግር ጋር በተገናኘም ስድስት ኩባንያዎች ችግር ገጥሟቸው ነበር:: የተወሰኑት አሁንም ወደ ሥራ አልተመለሱም:: እነዚህ አምራቾች ወደ ሥራ እንዲመለሱ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ ያነሳሉ።

የመሠረተ ልማት አለመሟላት፣ የሠላም እጦት፣ የግብዓት አቅርቦት አለመሟላት ዘርፉን እየፈተኑ ካሉ ችግሮች መካከል መሆናቸውን የሚያነሱት አቶ ቴዎድሮስ፤ ስትራቴጂው በዘርፉ የሚስተዋሉ ዋና ዋና ተግዳሮቶችን በመፍታት ሀገሪቱ በሆርቲካልቸር ኢንዱስትሪው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፎካካሪ እንድትሆንና ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ እንዲያድግ ያግዛል የሚል ተስፋ ተጥሎበታል ይላሉ::

ለኢንዱስትሪዎች በቂ የግብዓት አቅርቦት እንዲኖር በማድረግም አጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ የሚኖረውን አስተዋፅዖ ለማሳደግ እንደሚያስችል ይጠቁማሉ።

ኢትዮጵያ ለአትክልትና ፍራፍሬ እምቅ አቅም ቢኖራትም እስካሁን በዘርፉ ከሚገኘው የውጭ ምንዛሪ አብዛኛውን የሚይዘው አበባ መሆኑን የሚናገሩት ዳይሬክተሩ፤ የዓለም የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የከተሜነት መስፋፋት የአትክልትን ፍራፍሬ ፍላጎት እንዲጨምር እያደረገ በመሆኑ ያለንን አቅም አሟጦ በመጠቀም የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ።

የሆርቲካልቸር ምርቶች በተፈጥሯቸው በቶሎ የሚበላሹ ናቸው:: በመሆኑም ማቀዝቀዣ የተገጠመላቸው መጋዘኖችና የጭነት መኪኖች ያስፈልጋሉ:: በዚህ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችም በአፋጣኝ መፈታት እንዳለባቸው ያስረዳሉ::

በስትራቴጂው የፋይናንስና የመሬት አቅርቦት፣ የግብዓት አቅርቦት ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች ይፈታሉ የሚል እምነት እንዳላቸው የሚጠቅሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህን ማድረግ ካልተቻለ የምንፈልገውን ውጤት ማግኘት አንችልም ይላሉ::

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ሶፍያ ካሣ (ዶ/ር)፤ እንደሀገር ያለው የሆርቲካልቸር አቅም ከፍተኛ ቢሆንም በተለይ ከውጭ ምንዛሪ አንጻር እያበረከተ ያለው አስተዋፅዖ በቂ አይደለም:: ለዚህም ከዚህ ቀደም የነበረውን የሆርቲካልቸር ስትራቴጂ የመከለስ ሥራ መሠራቱን ይገልጻሉ::

ስትራቴጂውን በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማስፈጸም 24 ቢሊዮን ዶላር ያስፈልጋል የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ይህም መሠረተ ልማትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን ለማሟላት ይውላል:: ገንዘቡም ከመንግሥት፣ ከግል ዘርፉና ከአጋር አካላት ድጋፍ የሚገኝ ይሆናል ይላሉ::

በባለሀብቶች ተይዞ ያለማ መሬት ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ቢገባ ከአበባ ብቻ ተጨማሪ 100 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እናገኛለን የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በአሁኑ ሰዓት በሆርቲካልቸር አልሚዎች የተያዘው መሬት 27 ሺህ ሄክታር መሬት ይደርሳል:: ከዚህ ውስጥ ወደ ሥራ እየለማ ያለው 21 ሺህ ሄክታር ብቻ ነው:: ይህን መሬት ወደ ልማት እንዲገባ የመደገፍ፣ መከታተልና መቆጣጠር ሥራ ያስፈልጋል ሲሉ ያስረዳሉ::

የዘርፉ ተዋንያን ስትራቴጂውን በመጠቀም በሆርቲካልቸር ልማት ላይ ያሉትን ተግዳሮቶች መቅረፍ እንደሚያስፈልግና ምርታማነትን በማሳደግ የአገር ኢኮኖሚን ማጎልበት እንደሚገባ ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ሁሉን አቀፍ ድጋፍ የሚሻው የሆርቲካልቸር ዘርፍ

**ማህሌት አብዱል**



በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካላቸው የልማት ዘርፎች መካከል የሆርቲካልቸር ልማት ይጠቀሳል:: ይህ ንኡስ ዘርፍ በተለይም ባለፉት ሁለት አስር ዓመታት ለዜጎች የሥራ እድል ከመፍጠር፣ የምግብና የሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ እና የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ከማሳደግ አኳያ ጉልህ አስተዋፅኦ አበርክቷል::

የግሉ ዘርፍ የግብርናው ዘርፍ ተሳትፎ በፍጥነት እያደገ እንዲመጣም የበኩሉን ሚና እየተወጣ ነው፤ የእድገት ፍጥነቱን ከማስቀጠል አኳያ ግን ተግዳሮቶች እያጋጠሙት ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: የዘርፉ ምርትና ምርታማነት እየቀነሰ ለመምጣቱ እንዲሁም በውጭ ምንዛሬ ግኝት ላይ የነበረው ድርሻ እየተንሸራተተ ስላለበት ሁኔታ የሚጠቀሱ ተግዳሮቶች እንዳሉ እየተጠቆመ ነው:: ከተግዳሮቶቹም መካከል እንደ ሀገር የሰላም እጦትና የተረጋጋ ሁኔታ አለመኖር፣ የመልካም አስተዳደርና የመሠረተ ልማት ችግሮች በዋናነት ይጠቀሳሉ::

መንግሥት የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት ሲያከናውናቸው ከቆዩ ተግባሮች መካከል በ2010 ዓ.ም በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀው ብሔራዊ የሆርቲካልቸር ስትራቴጂ አንዱ ነው:: ይህ ረቂቅ ሰነድ ግን እስከ አሁንም ሳይጸድቅ ቆይቷል:: በአሁኑ ወቅት ሰነዱን የመከለስ ሥራ እየተካሄደም ይገኛል::

በዚህ ሰነድ ላይ የሚነጋገር መድረክ በቅርቡ በተካሄደበት ወቅት የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ረቂቅ ሰነዱን መከለስ ያስፈለገው ዘርፉ ለሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ በማለም ነው:: ሚኒስቴሩ ስትራቴጂውን በማዘጋጀትና የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ባረጋገጠ መልኩ በማዳበር መተግበር አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ የውይይት መድረኮችን ሲያካሂድ ቆይቷል::

ስትራቴጂውን አሁናዊ ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ባገናዘበ መልኩ በመከለስ መዘጋጀቱን ሚኒስትሩ ጠቅሰው፣ የንኡስ ዘርፉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ሀገሪቱ ያላትን አቅም በመለየትና በአርሶ አደሮችና በግል ባለሀብቶች እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን ለመደገፍ እንደሚያስችል አመልክተዋል:: የድህረ ምርት ብክነትን ለመቀነስና ለሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ገበያ ጥራት ያለው ምርት ለማቅረብ ሀገራዊ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ እንዲያስችል ተደርጎ መዘጋጀቱንም ይጠቅሳሉ::

ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ በሆርቲካልቸር ንኡስ ዘርፍ የአበባ፣ አትክልትና እፀ ጣዕም፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ልማትን ለማስፋፋት አርሶ አደሮችና በግል ባለሀብቶች የሚሰሩ ሥራዎችን በመደገፍ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተደረጉ ጥረቶች ቢኖሩም፣ የንኡስ ዘርፉን ፀጋዎች በሚፈለገው ደረጃ ለመጠቀም በማምረትና በግብይት ሥርዓት ሂደት ያሉ ተግዳሮቶችን በመለየትና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ላይ ውስንነቶች ይታያሉ::

ይህም በመሆኑ እንደ ሀገር ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ እየቀነሰ መምጣቱን አመልክተው፣ ለእዚህም « ዘርፉ ካለፈው በጀት ዓመት መጠነኛ ቅናሽ ያለው ገቢ በ2016 በጀት ዓመት /535 ሚሊዮን ዶላር ብቻ/ ያስገኘበትን ሁኔታ በአብነት ጠቅሰዋል::

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ሶፊያ ካሳ (ዶ/ር) በበኩላቸው በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከዘርፉ የተገኘው ገቢ እንደቀድሞውም ባይሆንም ብዙ ተስፋ የሚያስቆርጥ አይደለም ሲሉ ጠቅሰው፣ የግሉን ሴክተር ተሳትፎ ከፍ ማድረግ ከተቻለ በተሻለ መጠን የውጭ ምንዛሬ ግኝቱን ማሳደግ እንደሚቻልም ጠቁመዋል::

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ከምርት አንፃር ትልቁን ሽፋን የያዘው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ነው፤ የአበባ ምርት ግን በበጀት ዓመቱ አነስተኛ የሚባል ነው:: በሌላ በኩል አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ አደር አበባ ልማት ላይ አይሳተፍም፤ የፍራፍሬ ልማቱም ሰፊ የሚባል አይደለም፤ አሁን ላይ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብሩና እንዲሁም አርሶ አደሩና ክልሎችም ባላቸው ኢኒሼቲቭ የፍራፍሬ ልማት እድገቱ ከፍ እያለ ቢሆንም ገና ብዙ ሥራ መሥራት ይጠበቃል:: በእሱ ልክ ግን የገበያ ተደራሽነት ላይ እየተሠራ ባለመሆኑ ዘርፉ ለሀገር እድገት የሚጠበቅበትን ሚና እንዳይወጣ ሆኗል::

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሆርቲካልቸር ዘርፉ በወጪ ንግድ ሰፊ ድርሻ እንደነበረው ሚኒስትር ዴኤታዋ ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት ወደ ውጭ የሚላከው አበባ መጠን ቀንሷል ብለዋል:: እንደ አቦካዶ ያሉ ፍራፍሬዎችና ማዕዛማ ሰብሎች በተወሰነ ደረጃ ወደ ሶማሊያና ጅቡቲ እንዲሁም በጣም ጥቂት ደግሞ ወደ መካከለኛው ምስራቅ ይላካሉ ያሉት ዶክተር ሶፊያ፣ ይህም ቢሆን ካለው ትልቅ አቅም አኳያ የሚላከው ምርት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም ብለዋል::

እሳቸው እንዳሉትም፤ ለሆርቲካልቸር ዘርፉ አፈፃፀም ደካማ መሆን በርካታ ችግሮች በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ:: የመሬት አቅርቦት፣ የመሠረተ ልማት በተለይም የመንገድ፣ የኃይል አቅርቦት ችግሮች ይስተዋላሉ:: አንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ጎርፍ በስፋት ስለሚከሰት አምራቾችን ከሥራ ውጭ የሚያደርግበት ሁኔታ ይታያል::

የፋይናንስ እጥረት ሌላው የዘርፉ ተግዳሮት መሆኑንም ጠቁመው፣ የግብዓትና አቅርቦት ለማሟላት ፋይናንስ ወሳኝ መሆኑን አመልክተዋል፤ ከዚህም አንጻር ውስንነት እንዳለ ጠቅሰዋል:: «በተለይ አዳዲስ ዘርፉን ለሚቀላቀሉ አካላት በቂ የፋይናንስ አቅርቦት አለመኖር፣ የገበያና የዲጂታል መረጃ ሥርዓት ውስንነት፤ የማበረታቻ ሥርዓት አለመዘርጋቱና የመልካም እርሻ አስተዳደር አለመኖር አልሚዎች በስፋት እንዳያመርቱ ማነቆ መሆናቸውን አመልክተዋል::

ሚኒስትር ዴኤታዋ በመሬት አቅርቦት ላይ የሚታየው ችግርም ዋነኛው የዘርፉ ተግዳሮት መሆኑን ተናግረው፣ በተለይ አማራ ክልል ላይ ለሆርቲካልቸር ልማት የታሰበ መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ የተደረገበት ሁኔታ አለ» እንዳለ ጠቅሰዋል:: ይህ መሬት ለአልሚዎች በጊዜው እንዲተላለፍ ባለመደረጉ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ መደረጉን ያስረዳሉ:: መሬቱ የሆርቲካልቸር ልማት በክላስተር ለመሥራት በአማራ ክልል ታስቦ የተዘጋጀ እንደነበር ያመለክታሉ::

ይህን አብነት ጠቅሰው ሲያብራሩም የአማራ ክልሉን የቆንዝላ ሆርቲ ፓርክ ጠቅሰዋል:: በአካባቢው ወደ 155 ሄክታር መሬት ለአልሚዎች መተላለፍ ሲገባው አለመተላለፉ እንደ ሀገር ለታየው ደካማ አፈፃፀም አብይ ምክንያት እንደሆነም ጠቅሰዋል:: ችግሩ ከስድስት ዓመታት ላላነሰ ጊዜ የዘለቀ መሆኑን ጠቁመው፤ «ከዚህ ቀደም በከፍተኛ አመራር ደረጃ ችግሩ በአጭር ጊዜ እንዲፈታ አቅጣጫ ተቀምጦ ስምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም እስካሁን ግን መፍትሔ አላገኘም» ሲሉ ያነሳሉ::

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ መሬቱ ለአልሚዎች ላለመተላለፉ በርካታ ችግሮች በምክንያትነት ይጠቀሳሉ:: የኃይል አቅርቦት፣ የ21 ኪሎ ሜትር መንገድ ግንባታ አለመጠናቀቅ፣ የፀጥታ ችግር መሬት ለአልሚዎች እንዳይተላለፍ ካደረጉት መካከል ይጠቀሳሉ:: በእነዚህ ችግሮች ምክንያት 32 ሺ ቶን ምርት ሳይገኝ ቀርቷል፤ ከዚህ ይገኝ የነበረ 140 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት አልተቻለም:: ከ4ሺ 80 በላይ የሥራ እድል መፍጠር አልተቻለም::

ዶክተር ሶፊያ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ በማጠናቀቅ ፣ የኃይል አቅርቦቱንም በማስፋፋትና መስኖውን በማገናኘት፣ የተጀመረውን የ21 ኪሎ ሜትር መንገድ ዝርጋታ በመጠናቀቅ መሬቱን በአፋጣኝ ወደ ልማት ማስገባት እንደሚገባ ያስገነዝባሉ:: ወደ መሬት ባንክ የተመለሰውን መሬትም ለባለሀብቶች በአግባቡ ማስተላለፍ ይገባል ይላሉ:: ለእዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ባለስልጣን እና የአማራ ክልል የሚመለከተው አካል በቀጣይ በጀት ዓመት ኃላፊነታቸውን ወስደው መሥራት እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል:: በማምረት ሂደት ላይ ያሉ ኩባንያዎችም የመሬታቸውን አቅም አሟጠው ያለመጠቀም ችግር እንደታየባቸውም ተጠቁሟል::

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ እንደ ሀገር በሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ 138 ኩባንያዎች ያሉ ሲሆን፣ 27 ሺ 629 ሄክታር የሚለማ መሬት አለ:: ከዚህ ውስጥ 21ሺ 718 ሄክታር ነው የለማው፤ 5ሺ 911 ሄክታሩ አለማም:: ከዚህ ውስጥ አንድ ሺ 300 ሄክታሩ የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል ነው:: ይህንን መሬት ወደ ልማት ለማስገባት ከአልሚዎችና ከክልሎች ጋር መግባባት ተፈጥሮ እየተሠራ ነው::

መሬቱ ያለማበት ምክንያትም ተለይቷል፤ አንዳንዱ አልሚ መሬቱን ከያዘ በኋላ ሌላ ፍላጎት የሚያማትርበት ሁኔታ እንዳለ ታውቋል:: የአበባ ገበያ መቀዛቀዙን ተከትሎ ወደ እንጆሪ ልማት የዞሩ አልሚዎች መኖራቸውን ጠቁመው፤ «በተለይም የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ ፍቃድ ሰጥቷቸው ወደ እንጆሪ ልማት የገቡ ኩባንያዎች አሉ» ይላሉ::

በአቅም ውስንነት፣ በሎጅስቲክ እጥረትና በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ በፀጥታ ችግር ምክንያት አልሚዎቹ በሙሉ አቅማቸው እንዳያለሙ መሆናቸውን ሚኒስትር ዴኤታዋ ጠቁመዋል:: «በእነዚህ ምክንያቶች በአበባ ብቻ ቢያንስ ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ አጥተናል፤ ይህ እጅግ ያስቆጫል፤ አቅሙም ሀብቱም እያለ ያለመሥራታችን ውጤት ነው» ሲሉም ይናገራሉ:: ሆኖም ከ2017 ጀምሮ ለልማት ያልዋለውን መሬት ወደ ልማት ማስገባት ከተቻለ ከእቅዱም በላይ የውጭ ምንዛሬ ማስገባት የሚቻልበት እድል እንዳለ ጠቁመዋል::

በመድረኩ ለዚህ የመፍትሔ ሃሳብ ተብሎ የተቀመጠው የኩባንያዎችን የመሬት አጠቃቀም ወቅታዊ በማድረግና የቀረቡ ጥናቶችን በማደራጀት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ ነው:: አሁን ከእያንዳንዱ ኩባንያ ጋር የማነበብ ሥራ እየተሠራ በመሆኑ የቀረውን መሬት ወደ ልማት መግባት ይገባዋል የሚል አቅጣጫ ተይዞ እየተሠራ መሆኑም ተጠቁሟል::

ዶክተር ሶፊያ «በቀረበው የዳሰሳ ጥናት መሠረት ውሳኔው ቀላል ሊሆን ይችላል፤ ግን መሬቱ ለሌላ አላማ ይዋል ሳይሆን አምራቾቹን በመደገፍ በትክክል ወደ ልማት እንዲገቡ ማድረጉ ነው ተመራጭ የሚሆነው» ሲሉም ያስገነዝባሉ:: ይህንንም ግብርና ሚኒስቴር፣ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤ የክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ በጋራ ሆነው ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ ልማት እንዲገቡ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ባይ ናቸው::

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ማብራሪያ፤ ለኢንቨስትመንት ቦታ የተሰጣቸውና በአበባ ልማት ላይ ተሰማርተው በኤክስፖርት ምርት ሙከራ ላይ የነበሩ ኩባንያዎች ሥራ ያቆሙ አሉ፤ ከእነዚህም መካከል በአማራ ክልል በተከሰተው የፀጥታ ችግር ሥራ ያቆመው አቢሲኒያ የተባለ ኩባንያ ይጠቀሳል:: በዚሁ ክልል ቆቦ አካባቢም ሰባት አትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች ሥራ ያቆሙበት ሁኔታ እንዳለ ተጠቁሟል::

«በእነዚህ ምክንያቶች ብቻ 17 ሺ 920 ቶን አትክልትና ፍራፍሬ ሳይለማ ቀርቷል ፤ በዚህም ወደ 14 ሚሊዮን ዶላር የሚሆን ገቢ ማጣት ውስጥ ተገብቷል» የሚሉት ዶክተር ሶፊያ፤ ያለማውን መሬት ወደ ሥራ ለማስገባት መሬቱ ያለበትን አካባቢና የአልሚውን ሁኔታ በማጥናትና በድጋሚ በማደራጀት የውሳኔ ሃሳብ መስጠት እንደሚገባ አስገንዝበዋል:: እነዚህ ኩባንያዎች ማልማት የማይችሉ ከሆነ ከክልሎች ጋር በመነጋገር መሬቱ ወደ ሌሎች አልሚዎች እንዲተላለፍ ማድረግ ይጠበቃል ሲሉም ጠቁመዋል:: በተቻለ መጠን እስከ አራተኛው ሩብ ዓመት ድረስ መፍትሔ ሊሰጣቸው ይገባል የሚል አቅጣጫ መያዙንም ነው ያመለከቱት::

በሌላ በኩል ባለሀብቶችን በዘርፉ ኢንቨስት ለማድረግ የከፈሉበትን መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያለመስጠት ሁኔታ በዘርፉ ተዋናዮች እንደ ትልቅ ተግዳሮት ይነሳ እንደነበር አስታውሰው፤ በዚህ ረገድ በተለይም በኦሮሚያ ክልል ይነሳ የነበረው ቅሬታ በአሁኑ ወቅት ምላሽ ማግኘቱን አስታውቀዋል:: ከመሠረተ ልማት አኳያ የሚነሱ ቅሬታዎችንም በተለይ የኃይልና የቴሌኮም አቅርቦት ችግርን ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመልክተው፣ በዚህም የበርካታ ኩባንያዎች ቅሬታ በተናጠል የተፈታላቸው መሆኑን ተናግረዋል::

ጎርፍ በቢሾፍቱ፣ ሰበታና ወልቂጤ አካባቢ ከፍተኛ ችግር እያስከተለ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታዋ አንስተው፤ «ቢሾፍቱ ከባቡር መንገድ ግንባታው ጋር ተያይዞ የጎርፍ ችግር አለ:: ለዚህ ችግር ባለቤቱ ማነው የሚለውን ጥያቄ በተደጋጋሚ አንስተናል፤ ባለሀብቶቹም ችግሩን ለመፍታት ለመተባበር ፈቃደኛ ናቸው፤ በቀጣይ ዓመት የሚፈቱበት ሁኔታ መፈጠር አለበት» በማለት ተናግረዋል::

«ግን ቋሚ መፍትሔ የሚፈልግ በመሆኑ በመንግሥት በኩል ቁርጠኝነቱ አለ፤ እየተሠራም ነው::»» ሲሉም አስታውቀዋል:: ሁሉም ችግር በመንግሥት እንደማይፈታ ጠቁመው፣ የግል ባለሀብቱ የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከት መቻል እንዳለበትም አስገንዝበዋል::

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር መለስ መኮንን የሆርቲካልቸር ዘርፉን ችግር ለመፍታትም የዘርፉ አንኳር ችግሮችና የመፍትሔ ሃሳቦችን ያጠቃለለ ብሔራዊ የአስር ዓመት ረቂቅ ስትራቴጂ መዘጋጀቱን ጠቅሰዋል:: ዘርፉ አሁን ለ200 ሺ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠሩን ገልጸው፣ የስትራቴጂው ትግበራ በሚጠናቀቅበት 2026 ላይ ቁጥሩን ወደ ሁለት ሚሊዮን ለማሳደግ ይሰራል ብለዋል::

በመድረኩ ላይ የተሳተፉ የዘርፉ ተዋናዮች በበኩላቸው ሀገሪቱ በሆርቲካልቸር ዘርፍ የሚገባትን ያህል ገቢ እንድታገኝ ከተፈለገ ከመሠረተ ልማት፣ ከፀጥታና ከመልካም አስተዳደር ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት መንግሥት በቁርጠኝነት ሊሠራ እንደሚገባ አስገንዝበዋል:: በተለይ ችግሩን ተቋቁመው እያለሙ ያሉ ባለሀብቶችን በመደገፍ ምርታማነታቸው እንዲጎለብትና የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ግኝት አሁን ከሚገኘው በላይ በላቀ ሁኔታ እንዲጨምር መሥራት ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል::

ማህበራዊ

# አስኳላ

## የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር



**ብርሃን ፈይሳ**

የዓለም የሥልጣኔ ዕድገት መለኪያው ኢንዱስትሪ ነው። ለዚህም ነው ዘመናዊ የዓለም ታሪክ ሲወሳ መነሻውን ከኢንዱስትሪ አብዮት የሚያደርገው። የኢንዱስትሪ አብዮት የአውሮፓ ሀገራትን ያነቃቃ፣ የዘመናዊ ሥልጣኔ መነሻ የሆነ፣ በአጠቃላይ አሁን ላለው የሰው ልጅ የአኗኗር ዘይቤ መሠረት የጣለ ነው። ይህ የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ እያደገ መጥቶ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ለመካተት በቅቷል። የበለጸጉት ሀገራት ደግሞ ይህንን የኢንዱስትሪ አብዮት በአግባቡ በመጠቀም ወደ ፈጣን የቴክኖሎጂ ውጤቶች መገኛነት አሳደጉት። ከዘመናነት ጉዞ በኋላም በተለያየ ባሕላዊ መንገድ ከትውልድ ወደትውልድ ሲሸጋገር የኖረውን እውቀት «ተግባር ተኮር» ትምህርት ተብሎ ለሥራ ፈጠራ አጋዥ እንዲሆን አገልግሎት ላይ መዋል ጀመረ።

ለ19ኛው ክፍለ ዘመን የብልጽግና በረከቶች ፈር ቀዳጁም ኢንዱስትሪ መስፋፋት ሲሆን፤ የሀገራትን ኢኮኖሚ ማደግ ተከትሎም ለስልጣኔ ከፍተኛ ሚናን ለመጫወት በቅቷል። እንደ ቻይና፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ታይዋን፣... የመሳሰሉ ሀገራት ላስመዘገቡት ፈጣን እድገት ተጠቃሽም ነው። የኢንዱስትሪ ዘርፍ በሀገራት ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ሚና ከመጫወቱም ባለፈ፤ ምርቶችን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ቀጣይነት ያለው የገቢ ምንጭ በመሆንም እያገለገለ ይገኛል። የዜጎችን አኗኗር በማሻሻልና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድም ያደጉ ሀገራት ከዘርፉ ብዙ ተጠቅመዋል። በተጨማሪም ሰዎች በጉልበት ያከናውኗቸው የነበሩ ሥራዎችን በቴክኖሎጂ በመተካት ድካምን ቀንሶ ቅልጥፍናን በመጨመር ምርትንና ምርታማነትን ለማሳደግ በቅቷል። በሥራ እድል ፈጠራውም ረገድ ዛሬም ድረስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል።

ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ስንመጣ ግን የምናገኘው ታሪክ ካደጉትም ሆነ በማገድ ላይ ካሉ ሀገራት ጋር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ባጭሩ ከዘርፉ ከምንፈልገው ምርትና ምርታማነት እንዲሁም የሥራ እድል ፈጠራ መጠቀም የቻልነው እጅግ በጣም ትንሽ ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን። ምክንያቱ ደግሞ የኢንዱስትሪው አለመስፋፋትና አለመጠናከር ሲሆን ይህንን ለመቅረፍ ደግሞ ከገንዘብ አቅም ባለፈ የተማረ የሰው ኃይል ማግኘት ትልቁ ጥያቄ ነው።

እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ በሀገሪቱ ይሰጡ የነበሩት ትምህርቶች ከተግባር ይልቅ የወረቀት ላይ ሆነው መቆየታቸው በቂ የሰው ኃይል ላለመገኘቱ አንዱ ምክንያት ነው። በዚህም የተነሳ ከቴክኒክና ሞያ የትምህርት ተቋማትና ከዩኒቨርሲቲዎች የሚመረቁ ተማሪዎችን ጨምሮ «የራሳቸው ሥራ ጀመሩ» ከተባለ የሚሰሩት አያት ቅድመ አያቶቻቸው በልማዳዊ መንገድ የፈጠሩትን ሥራ ነው። ይህ የሚያሳየን ኢንዱስትሪውና በመስኩ የሚሰለጥኑ ተማሪዎች መካከል የተሳለጠ ግንኙነት አለመኖሩን ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን በተለይም የኢንዱስትሪ ፓርኮችን መስፋፋትና የዘርፉንም እድገት ተከትሎ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የትኩረት አቅጣጫ ይህንኑ ማዕከል ያደረገ እየሆነ መጥቷል።

ከዚህ ቀደም በነበረው ተሞክሮ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከኢንዱስትሪዎች ሳይቀራረቡ በንድፈ ሃሳብ ትምህርት ብቻ ማተኮራቸው ሰልጣኞች ከተመረቁ በኋላ ወደ ኢንዱስትሪው ሲቀላቀሉ እንግድነት እንዲሰማቸው ሲያደርግ የነበረ ነው። በርግጥ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው በሥራ ልምምድ (አፓረንትሺፕ) ኢንዱስትሪዎቹ ውስጥ የመግባት እድል ይኖራቸዋል። ይሁንና በሚፈለገው መጠን ውጤታማ ሆነው የሥራውን ዓለም መቀላቀል ይሳናቸው ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ተማሪዎቹ አብዛኛውን ጊዜ በወረቀት ትምህርት ላይ አሳልፈው ለምረቃ ጥቂት ጊዜ ሲቀራቸው በውስን ሰዓት ከተግባራዊ ትምህርት ጋር የሚገናኙ በመሆናቸው ነው። በመሆኑም የትምህርት ተቋማቱ ከኢንዱስትሪው ዘርፍ ጋር የሚፈጥሩት ትስስር ይህንን ክፍተት ሊሸፍን የሚችል ሆኖ አልተገኘም። በአሁኑ ወቅት ግን እንደ መፍትሔ ሆኖ ችግሩን ለመቅረፍ እየተሰራበት ያለው የትምህርት ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር ትልቅ ተስፋ የተጣለበትና የብርሃን ጭላንጭል ያሳየም ለመሆን በቅቷል።

የኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ኢንዱስትሪ ትስስር ታሪክ በአንጻራዊነት ገና ጅምር ላይ ቢሆንም እያደገ ከመጣው ሰፊ የኢኮኖሚ ልማት እና የቴክኖሎጂ እድገት ጋር እየተጣጣመ የመጣ መሆኑን የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስትር መረጃ ያመላክታል። የከፍተኛ ትምህርት እና ኢንዱስትሪ ትስስር ከታሪክ አኳያ በዋነኛነት ያተኮረው በንድፈ ሃሳባዊ እውቀት ላይ ውስን በሆነ የኢንዱስትሪ ትብብር ላይ ነው። በ1950 ዎቹ ዓ.ም የተቋቋመው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በወቅቱ የነበሩት ኮሌጆችም ቢሆኑ ከኢንዱስትሪው ዘርፍ ጋር ያላቸው ግንኙነት እጅግ አነስተኛ ነበር።

የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተቀምጠው በትምህርት ተቋማትና በኢንዱስትሪ መካከል ያለውን ልዩነት የማጣጣም ሥራ የተጀመረው ከኢትዮጵያ ሚሊኒየም በኋላ ነው። ከዚህ ጊዜ አንስቶም የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ጅምር ሥራዎች ቢኖሩም በትምህርትና ስልጠና ተቋማትና በኢንዱስትሪው መካከል ውጤታማ ሥራ ተሰርቷል ለማለት አያስደፍርም። ዛሬም ድረስ መንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ለሀገራዊ ልማት ለማዋል ያለውን ቁርጠኝነት የሚያንፀባርቁ የዩኒቨርሲቲ እና የኢንዱስትሪ ትስስር ለማጠናከር የሚያስችሉ በርካታ የፖሊሲ ውጥኖችን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። እነዚህን የትስስር ሥራዎች በይዘታቸው እና ከባህሪያቸው አኳያ ውጤታማ እንዲሆኑ አስገዳጅ የሕግ ማዕቀፍ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም የለውጡ መንግሥት በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት እና የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ከኢንዱስትሪዎች ጋር የሚኖራቸውን ትስስር ለማጠናከር እና ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገቶች ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው በመገንዘቡ የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ቁ.1298/2015 የሕግ ማዕቀፍ አውጥቷል።

ይህንንም ተከትሎ ዩኒቨርሲቲዎች እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እና የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች አጋር አካላትን ለጋራ ጥቅም በትስስር ተግባራዊ ምርምር መሥራት ጀምረዋል። የትስስር አዋጁ በርካታ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የሕግ ማዕፎችን የትስስር ፖሊሲዎችን እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዱ የተማሪዎች የተግባር ልምምድ፤ የኤክስተርንሽፕ /የሠራተኞች የተግባር ተሞክሮ፤ የትብብር ስልጠና ፤ የማማከር አገልግሎት። እንዲሁም የጋራ ተግባራዊ ምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር መመሪያዎችን በከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና በኢንዱስትሪ መካከል ትስስርን የበለጠ ለማጥራት እና ውጤታማነት ለማሻሻል በመሰራት ላይ ይገኛሉ።

የትስስር መመሪያዎቹ የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎችን ተደራሽ እና ውጤታማ ከማድረግ አኳያ የተለያዩ የማበረታቻ ስልቶችን፣ የአእምሯዊ ንብረት አስተዳደርን እና ተግባራዊ የማህበረሰቡን ችግሮች የሚፈቱ በጋራ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን እና የፈጠራ ተግባራትን ጨምሮ ዝርዝር ሂደቶችን እና ደረጃዎችን ያስቀምጣል። በመሆኑም የትስስር አዋጁ የማህበረሰቡን ተግዳሮቶች የሚፈቱ የጋራ ተግባራዊ ምርምር፤ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የፈጠራ ሥራዎች እንዲሁም የኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ በመሥራት ላይ ይገኛል ለማለት ያስደፍራል።

የትስስር አዋጁ ዩኒቨርሲቲዎች የጋራ ምርምር አጀንዳዎቻቸውን ከሀገራዊ ልማት ግቦች እና ከኢንዱስትሪ ፍላጎቶች ጋር እንዲያቀናጁ እና ወጪ ቆጣቢ የሀብት አጠቃቀም እንዲኖር አግዟቸዋል። አዋጁ ለዩኒቨርሲቲዎች እና ለምርምር ተቋማት የተሻሻለ ሥርዓተ ትምህርት፤ አግባብነት ላይ የተመሠረተና ከኢንዱስትሪዎች የገበያ ፍላጎትና ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆንም አስችሎታል።

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እና ኢንዱስትሪዎች መካከል ያለው ትስስር የምርምር ውጤቶችን ከገበያ ፍላጎቶች ጋር በማጣጣም የተግባር ስልጠናዎችን፣ የጋራ የተግባር ልምምዶችን በመስጠት የኢንዱስትሪውን ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ማሳደግም አስችሏል። ይህም መንግሥት በከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እና በኢንዱስትሪዎች ልማትና ፈጠራ ላይ በትስስር ንቁ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበትን ነባራዊ ሁኔታ ለመፍጠር ያለውን ቁርጠኝነት የሚያንፀባርቁ ናቸው።

የትስስር አዋጁ በቀጣይ የትስስር ሥራዎችን ከማሳለጥ እና ውጤታማ ከማድረግ አንጻር የጋራ የምርምር መሠረተ ልማቶችን ለማሳደግ፣ የተሻሻሉ የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ከኢንዱስትሪዎች ጋር ለጋራ የቴክኖሎጂ እድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የትስስር ሥራዎችን ለማጠናከር ብሎም ለተማሪዎች፣ ለኢንዱስትሪዎች እና ለዩኒቨርሲቲዎች በጋራ ፈጠራና በኢኮኖሚ ዕድገት እና በህብረተሰብ ልማት ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያግዛቸው ይሆናል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከኢንዱስትሪው ጋር ሰፊ ቁርኝት ካላቸው የትምህርት ዘርፎች መካከል አንዱ ቴክኒክና ሙያ መሆኑ ይታወቃል። በተለያየ መስክ የሙያ ባለቤት እና የፈጠራ ምንጭ የሆነው ይህ ዘርፍ የሚያፈራው የሰው ኃይል ከኢንዱስትሪው ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው ነው። የቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና የኢንዱስትሪ ትስስር ታሪክ ከጣሊያን ወረራ በኋላ በ1942 ዓ.ም ተግባረ ዕድ የቴክኒክ ትምህርት ቤት ከመከፈት ጋር ጅማሬውን ያደርጋል። ከትምህርት ቤቱ መቋቋም በኋላም በአንጻራዊነት የቴክኒክና ሙያ አስፈላጊነት ላይ መጠነኛ የአመለካከት ለውጥ ሊመጣም ችሏል። ከአስርት ዓመታት በኋላም በ1990ዎቹ አዲስ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተዘጋጅቶ የስልጠና ዘርፉ ሥርዓት ተዘርግቶለት መሰጠት ተጀምሯል።

እንደ ሀገር የተጀመሩ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ፣ ተኪ ምርቶችን የማስፋት፣ ምቹና ዘላቂ የሥራ ዕድል እንዲሁም ሰላማዊ ኢንዱስትሪ የመፍጠር ዕቅዱን ለማሳካት የሰለጠነና የበቃ የሰው ኃይል መኖር የግድ ነው። የኢንዱስትሪዎች ተወዳዳሪነት የሚወሰነው ደግሞ ብቃት ባለው የሰው ኃይል እንደመሆኑ ዘርፉ ያሉበትን ፈተናዎች ለማለፍ፣ የአመለካከት ችግሮችን መቅረፍ ከቻለ የኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ። ብሎም ከውጭ የምናስገባቸውን ምርቶች በራሳችን የማምረት አቅም ለመተካትና ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና ለመጫወት ይረዳል። አሁን ባለው ሁኔታም በየጊዜው እየጨመረ ለመጣው የኢንዱስትሪዎች መስፋፋትና የሰው ኃይል ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት የስልጠና ዘርፉን ማጠናከር አስፈላጊ አጠያያቂ ጉዳይ አይደለም። ለዚህ ደግሞ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ማዕከላት በክህሎት የበቃ የሰው ኃይል ለማቅረብ የሚኖራቸው ሚና ቀዳሚውን ድርሻ ይወስዳል።

የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ከተለያዩ የኢንዱስትሪ ተቋማት እንዲሁም ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በመሆን በልዩ ትኩረት እየተሠራም ይገኛል። የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት በቅርቡ ተማሪዎቹን ባስመረቀበት ወቅትም ሚኒስትሯ ሙፈሪያት ካሚል ያነሱት ይህንኑ ነበር። ሚንስትሯ በንግግራቸው «እንደ ሀገር በዘርፉ የጀመርናቸውን የሪፎርም ሥራዎችን ለማቀጣጠል የሚያስችል እንደሆነ እምነቴ የፀና ነው» ብለዋል። በመሆኑም በስልጠና ቆይታችሁ ባገኛችሁት ክህሎትና በቀሰማችሁት እውቀት ለመጣችሁበት ማኅበረሰብ፣ አካባቢ፣ ተቋምም ሆነ ኢንዱስትሪ ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ለማበርከት ከወዲሁ እንድትዘጋጁ ሳሳስባችሁ ከአደራም ጭምር ነው።» የሚል መልእክት አስተላልፈዋል።

ይህን ያነሳነው የቴክኒክና ሙያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተገቢውን ክብርና ትኩረት እያገኘ መሆኑን ለመጠቆም ነው። ከዚህ በፊት በነበረው አመለካከት ቴክኒክና ሙያ ብዙም ትኩረት የሚሰጠው አልነበረም። የቴክኒክና ሙያ የንድፈ ሃሳብ ትምህርት ከሚሰጥባቸው የትምህርት ተቋማት በተሻለ ለኢንዱስትሪ መሠረት የሆነ ተቋም ነው። በተገቢው መንገድ ከተሠራበት ሀገር በቀል የሆኑ ሙያዎችን ወደ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ማስደግ የሚቻልበት ነው። ብዙ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች ተሰጥኦዋቸውን የሚጠቀሙበትን ዕድል የሚፈጥርበትም ቦታ ነው። በተጨማሪ ከመደበኛ ትምህርት ባለፈ ትስስሩ የባሕል አምራቾችንም ሊያጠቃልል እንደሚገባ ይነሳል። ሀገር በቀል የሆኑና በባሕላዊ መንገድ የሚመረቱ ብዙ ዓይነት ዕቃዎች አሉ። እነዚህን ዕቃዎች የሚያመርቱ ሰዎችን በማምጣት የተግባር ተሞክሮውን ለተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግም ይጠበቃል።

# ወቅታዊ

# "በችግር ውስጥ ሆነን ያስመዘገብነው ውጤት ለከተማው ነዋሪና ለአልሚ ባለሀብቶች ተስፋ የሚሰጥ ነው"

- አቶ ባዩህ አቡሀይ
የጎንደር ከተማ ከንቲባ



ፎቶ፡-እዮብ ተፈሪ

ሄለን ወንድምነው

የጎንደር ከተማ በ1632 ዓ.ም መመስረቷ ይነገራል:: አሁን ላይ በስድስት ክፍለ ከተማ፣ በ25 የከተማ ቀበሌ እና በ11 ቀበሌ በድምሩ በ36 ቀበሌ የተዋቀረች ናት:: አጠቃላይ የቆዳ ስፋቷም 31 ሺህ 400 ሄክታር ነው:: በዚህች ከተማ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ እንደሚኖርባት ይገመታል::

ጎንደር ለኢንቨስትመንት፣ ለንግድ እና ለቱሪዝም የተመቸች ከተማ ብትሆንም፤ ባለፉት ዓመታት የተፈጠሩ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች የከተማዋን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሲያስተጓጉሉ ቆይተዋል:: በአሁኑ ወቅት የከተማዋን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ወደ ነበረበት ለመመለስ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው::

አዲስ ዘመንም በዛሬው ወቅታዊ ዓምዱ ከጎንደር ከተማ ከንቲባ ጋር በከተማዋ አጠቃላይ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴን አስመልክቶ ቃለ ምልልስ አድርጓል:: ከከንቲባ ባዩህ አቡሀይ ጋር የተደረገው ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል:: መልካም ንባብ::

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት የጎንደር ከተማ አጠቃላይ የሰላምና ጸጥታ ሁኔታ እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው ምን ይመስላል?**

**አቶ ባዩህ፡- ጎንደር** ከተማ ለንግድና ለቱሪዝም የተመቸች ከተማ ናት:: እንደሚታወቀው በጎንደር ከተማ የፋሲል ቤተ መንግሥትን ጨምሮ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት የተመዘገቡ በርካታ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ይገኙባታል:: በዙሪያዋም ሊጎበኙ የሚችሉ የጣና ገዳማትና አብያተ ክርስቲያን እንዲሁም የሰሜን ፓርክ እና ሌሎች በርካታ ታሪካዊ ቦታዎች አሉ:: ለላሊበላና ለአክሱምም ማዕከል ሆና የምታገለግል ከተማ ናት:: የከተማዋ አካባቢ በኢንቨስትመንት ደረጃም በርካታ የሰብል ምርቶችና የቅባት እህሎች የሚመረትበት ነው::

እነዚህንና ሌሎች እንቅስቃሴዎችን መሠረት በማድረግ በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሲካሄድበት ቆይቷል:: ይሁን እንጂ ባለፉት ዓመታት ግጭቶች እየተፈራረቁ የከተማዋን አጠቃላይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ አስተጓጉሏል:: በተለይ ደግሞ ኮቪድ ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ቢሆንም ጎንደር ከተማ በቱሪዝም የተመሰረተች ከተማ እንደመሆኗ መጠን በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል::

በተጨማሪም የቅማንት አማራ የብሔረሰብ ግጭት ከተማዋ ብዙ ችግር ውስጥ እንድትገባ አድርጓታል:: ከዚያም ባለፈ ከዓመታት በፊት የተካሄደው የህልውና ዘመቻው በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የከተማችንን የቱሪዝም፣ የኢንቨስትመንት፣ የንግድ እና የሰላም ሂደቱን ሲያስተጓጉል መቆየቱ የሚታወስ ነው::

ከህልውና ዘመቻ ማግስትም በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ከወርሃ ሐምሌ 2015 ዓ.ም ጀምሮ ክልሉ ላይ በተፈጠረው ግጭት የከተማዋ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ችግር ውስጥ አስገብቶት ቆይቷል:: በከተማዋ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴውን ወደነበረበት ለመመለስ በርካታ ሥራዎችን ስንሰራ ቆይተናል::

በተለይም መከላከያ ሠራዊት፣ የአካባቢው የጸጥታ ኃይልና ማህበረሰቡ በሰሩት የቅንጅት ሥራ በከተማዋ አንጻራዊ ሰላም ከመስፈኑም ባለፈ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ከነበረበት መፋዘዝ ወጥተው ማንሰራራት ጀምረዋል::

ንግድንም በሚመለከት ጎንደር ከሲራራ ንግድ ጀምሮ የኮሪደር መውጫ ሆና ለዘመናት ትልቅ የንግድ እንቅስቃሴ የሚከናወንባት ከተማ ነበረች:: በግጭቱ ባለሀብቱ እና ነጋዴው አካባቢያቸውን ትተው እንዲሰደዱ እንዲሁም ከወልቃይት እና በዙሪያው ካሉ አካባቢዎች ጋር ያለው የንግድ ትስስር እንዲተስተጓጎል ምክንያት ሆኖ ነበር::

> **በከተማዋ አሁን የተገኘው አንጻራዊ ሰላም መከላከያ ሠራዊት እና የአካባቢው የጸጥታ ኃይል የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ከፍለው ያመጡት ነው**

ይሁን እንጂ አሁን እየተሠራ ባለው የሰላም ማስከበር ሥራ ባለሀብቶች ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱ እና ከወልቃይት እና በዙሪያው ካሉ አካባቢዎች ምርትና ሸቀጥ ወደ ከተማው እየገባ በመሆኑ የከተማዋ የንግድ እንቅስቃሴ ከነበረበት መፋዘዝ መውጣት የቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል::

የግጭት ትርፉ የሀገርን እድገት ማቀጨጭ፣ ማከሰርና ማጥፋት ነው:: ይህንን ለመቀልበስ እንደከተማ ሰፊ ሥራ በመሥራታችን አንጻራዊ ሰላም ማስፈን ተችሏል:: በቀጣይ የተገኘውን አንጻራዊ ሰላም ወደ ሙሉ ሰላም ለመቀየር ከፌዴራል ጀምሮ በሁሉም ደረጃዎች በርካታ ሥራዎችን እየሠራን ነው::

በስምንት ቀጣና ሕዝቡን በማወያየት እና የሰላም ካውንስል በማቋቋም ግጭቶች እና ችግሮች በውይይትና በድርድር እንዲፈቱ አቅጣጫ ተቀምጧል:: የተቀመጠውን አቅጣጫ ስኬታማ ለማድረግ ጫካ የገቡ አካላት ችግራቸውን ለውይይት እና ለድርድር በማቅረብ የከተማው ነዋሪ የተሟላ ሰላም አግኝቶ እጁን ወደ ልማት እንዲመልስ ማድረግ ይገባል::

እንደ ከተማ አስተዳደር ላለፉት ዓመታት ሕዝቡን ያማረሩ የመልካም አስተዳደር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታት ከደሴ ከተማ እና ከዙፋን ችሎት ተሞክሮ በመውሰድ የከንቲባ ችሎት መድረክ ተጀምሮ ለረጅም ዓመታት የቆዩ ችግሮችን መፍታት ተችሏል::

ጎንደር ከተማ ለንግድ፣ ለኢንቨስትመንት እና ለቱሪዝም እንቅስቃሴ ምቹ ከተማ በመሆኗ በቀጣይም የተገኘውን አንጻራዊ ሰላም ወደተሟላ ሰላም በመቀየር ሕዝቡን ያሳተፈ የሰላም ግንባታና የልማት ሥራዎች ትኩረት ሰጥተን እናከናውናለን::

**አዲስ ዘመን፡- ከለውጡ ወዲህ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ከማከናወን አንጻር የተሠሩ ሥራዎች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ባዩህ፡-** የጎንደርና የአካባቢው ነዋሪ ለውጡን ተከትሎ ይመጣል የሚል በርካታ የልማት ጥያቄ ነበራቸው:: በከተማው በተለያዩ ጊዜያት በሚፈጠሩ ግጭቶች በሚፈለገው ደረጃ ማልማት ባይቻልም በተጨባጭ ግን በአንድ በኩል ሰላም የማጽናት በሌላ በኩል ደግሞ በርካታ የልማት ሥራዎችን እየሠራን እንገኛለን::

ከሚሰሩት የልማት ሥራዎች መካከል መንገድ አንዱ ሲሆን፣ በዚህ ዓመት 22 ኪሎ ሜትር የሚደርስ ደረጃውን የጠበቀ የጠጠር መንገድ አጠናቀናል:: በቀጣይ ዓመት ወደ አስፓልት በመቀየር ደረጃውን ለማሻሻል አቅደናል:: በተጨማሪም በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ዘጠኝ ድልድዮች ገንብተን የማጠናቀቂያ ምዕራፉ ላይ ደርሰናል::

በከተማዋ የሚገኙት መንገዶች ከሰሜን ወደ ደቡብ የተዘረጉ በመሆናቸው ከምዕራብ ወደ ምስራቅ የሚያገናኙ መንገዶችና ድልድዮች አልነበሩም:: በዚህ ዓመት አቅደን እየሠራነው ያለው የመሠረተ ልማት ሥራ የከተማዋን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሊያሳልጡ የሚችሉ ናቸው:: በተለይ ግንባታቸው እየተጠናቀቀ የሚገኙት ዘጠኝ ድልድዮች የከተማዋን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሊያሳልጡ የሚችሉ ናቸው::

ጎንደር የምትታወቅበት የበዓላት ወቅት ሲመጡ የሚያጋጥመውን የመንገድ መጨናነቅ ሊቀርፉ የሚችሉ አማራጭ መንገዶች ተገንብተዋል:: በሌላ በኩል የከተማዋን ጽዳት እና ውበት ለማስጠበቅ ከ600 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ የቄራ ግንባታ የሲቪል ሥራው አልቆ የኤሌክትሮ መካኒካል ገጠማው እየተከናወነ ነው፤ በቅርብ ጊዜያት ግንባታው ተጠናቆ ለምረቃ ይበቃል ተብሎም ይጠበቃል::

በተጨማሪም ካለፉት የለውጥ ዓመታት ጀምሮ በርካታ ትላልቅ እና አነስተኛ የወጣት መናፈሻዎች፣ የገበያ ማዕከላት፣ መናኸሪያ፣ የጌጠኛ ውስጥ ለውስጥ መንገድ እና ሌሎች ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ነው::

በየዓመቱ ከ20 ኪሎ ሜትር በላይ የጌጠኛ ጠጠር መንገድ እየተሠራ ያለበት ሁኔታ አለ:: በቀጣይም ፕሮጀክት መጀመር ብቻ ሳይሆን ማጠናቀቅን ባሕል ለማድረግ በራሳችን አቅም በርካታ ፕሮጀክቶችን ለመገንባት አቅደናል::

ከለውጡ ዓመታት በፊት ተጀምረው ሲጓተቱ የነበሩ ፕሮጀክቶች በተለይ ከአዝዞ አርበኞች አደባባይ የነበረው የአስፓልት መንገድ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በፍጥነት እንዲጠናቀቅ ባስቀመጡት አቅጣጫ መሠረት ግንባታው በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል::

በተጨማሪም ለከተማው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ትልቅ ፋይዳ አላቸው ተብሎ የሚገነቡ እንደ መገጭ ዓይነት ድልድዮች እና የንጹህ መጠጥ ውሃ ችግርን ሊቀርፉ የሚችሉ ፕሮጀክቶች በፌዴራል መንግሥት ትኩረት ተሰጥቷቸው ግንባታቸው እየተከናወነ ይገኛል::

**አዲስ ዘመን፡- የከተማዋ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? በተለይ ምርትን በሀገር ውስጥ ከመተካት፣ የውጭ ምንዛሬን**

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

## "በችግር ውስጥ ሆነን ያስመዘገብነው ውጤት ለከተማው ነዋሪና ...

ከገጽ 9 የዞረ



**ከማስገኘት እና የሥራ እድል ከመፍጠር አንጻር እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ምን ምን ናቸው?**

**አቶ ባዩህ፡-** ባለፉት ስድስት ዓመታት ጎንደርን የኢንቨስትመንት ተመራጭ ከተማ በማድረግ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ጎንደር እና አካባቢው በርካታ የቅባት እህሎች፣ ቅመማቅመም እና ሌሎች የሰብል ዓይነቶች በስፋት የሚመረትበት በመሆኑ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ እና ለእንስሳት ሀብት ልማት ምቹ አካባቢ ነው፡፡

ባለፉት ዓመታት በክልሉ እና በከተማው አቅም አምስት የኢንዱስትሪ መንደሮችን ከልለናል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አራቱ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ መሠረተ ልማት ተሟልቶላቸው ለባለሀብቶች ተላልፈዋል፡፡ ኢንዱስትሪ መንደር ቁጥር አምስት ደግሞ ባለሀብቱ ካሳ እየከፈለ የሚወስደው እና እያስተላለፍን እንገኛለን፡፡ በአምስቱም የኢንዱስትሪ መንደሮች 46 በቅድመ ግንባታ፣ 137 በግንባታ ላይ፣ ግንባታ ያጠናቀቁ 70፣ በምርት ላይ ያሉ 192 በአጠቃላይ 445 ፕሮጀክቶች ይገኛሉ፡፡ ከመካከለኛ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ 192 ኢንዱስትሪዎች ሥራ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

ትኩረት ሰጥተን እየሰራንበት ያለው በርካታ ባለሀብቶችን መሳብ በመሆኑ በዚህ ዓመት ብቻ 116 ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 349 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመስጠት 92 ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት ለ105 ባለሀብቶች ማስተላለፍ ችለናል፡፡

በጎንደር ከተማ ያለው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ ነው፡፡ በተያዘው ዓመት ብቻ 27 ፕሮጀክቶችን ወደ ምርት ለማስገባት አቅደን 23ቱ ምርት ማምረት ጀምረዋል፡፡ ሰባት ፕሮጀክቶች ደግሞ ማሽን ተከላ ላይ ያሉና በቅርቡ ለማስመረቅ ዝግጅት ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

ኢንዱስትሪዎች እንደ ሀገር የሚገጥመውን የውጭ ምንዛሬ እጥረትን እንዲፈቱና ምርትን በሀገር ውስጥ እንዲተኩ ትኩረት አድርገን እየሰራን በመሆናችን በዚህ ዓመት ስምንት ኢንዱስትሪዎች 18 ሺህ 328 ቶን ምርትን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ 49 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማስገኘት ችለዋል፡፡

ተኪ ምርትንም በሚመለከት በተያዘው ዓመት ብቻ 12 ሺህ 799 ቶን ምርትን በሀገር ውስጥ ለመተካት ታቅዶ 29 ሺህ 888 ቶን ምርት በሀገር ውስጥ ማምረት ተችሏል፡፡ ኢንዱስትሪዎች ሲስፋፉ የከተማውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከማሳላጥ ባለፈ የውጭ ምንዛሬን ለማስገኘት፣ ተኪ ምርትን ለማምረትና የሥራ እድል ለመፈጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ በዚህ ዓመት ወደ ሥራ እየገቡ ባሉ ኢንዱስትሪዎች ብቻ ለአምስት ሺህ 71 ወጣቶች የሥራ እድል ተፈጥሯል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት ለወጣቶች የሥራ እድል ከመፍጠር፣ ምርትን በሀገር ውስጥ ከመተካት እና የውጭ ምንዛሬን ከማስገኘት አንጻር እንዲሁም ከተማው ካለው እድልና ከሚፈልገው የመልማት አቅም አንጻር ጥሩ ነው ተብሎ ባይወሰድም ካለው የጸጥታ ችግር አንጻር ያስመዘገበው ውጤት ለከተማው ነዋሪ እና ለአልሚ ባለሀብቶች ተስፋ የሚሰጥ ነው፡፡

በከተማዋ የገጠመን ችግር የወጣቶች ሥራ አጥነት እና የኑሮ ውድነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ይህንን መቅረፍ የሚያስችሉ ሥራዎች ትኩረት ሰጥተን ከሰራንባቸው ዘርፎች የወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራ ነው፡፡ በተያዘው ዓመት 46 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል እንፈጥራለን ብለን 45 ሺህ 248 ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ችለናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአረንጓዴ ዐሻራ፣ በሌማት ትሩፋትና በከተማ ግብርና መርሐግብር ማሕበረሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ባዩህ፡-** እንደ ሀገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከተቀመጡ አቅጣጫዎች አንዱ የሌማት ትሩፋት ነው፡፡ እኛም በከተማ ደረጃ የሌማት ትሩፋት መርሐ ግብርን ወደ ተግባር ማስገባት ችለናል፡፡ የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ጽሕፈት ቤት ብለን በአዲስ በማደራጀት ወደ ሥራ አስገብተናል፡፡ በዚህም በመርሐ ግብሩ የከተማውን የምግብ ዋስትና በተለይ በሥጋ፣ በእንቁላል፣ በወተት እና በማር የተትረፈረፈ ምርት እንዲኖር ለማድረግ በተሠራው ሥራ ተጨባጭ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

ለአብነት ጽላተማርያም የዶሮ እርባታና ማቀነባበር ከቤቷ ጀምራ አሁን ላይ በ100 ሺህ የሚቆጠሩ ዶሮዎችን ማርባት ችላለች፡፡ በዚህም በከተማው የነበረውን የእንቁላል ዋጋ ከ15 ብር ወደ ዘጠኝ ብር እንዲወርድ ተደርጓል፡፡ የእንቁላል ገበያ ከማረጋጋት ባለፈም ለበርካታ ወጣቶች የሥራ እድል ፈጥራለች፡፡ ሌሎች በርካታ ወጣቶችም በዘርፉ ተሰማርተው የከተማውን የእንቁላል ምርት በከፍተኛ ሁኔታ እያሳደጉት ይገኛል፡፡

በተያዘው ዓመት 665 ነጥብ ስምንት ቶን ሥጋ ለማምረት ታቅዶ አንድ ሺህ 64 ነጥብ ስምንት ቶን ሥጋ ማምረት ተችሏል፡፡ 23 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን እንቁላል ለማምረት ታቅዶ 30 ሚሊዮን እንቁላል ማምረት የቻልንበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

የወተት ላምም ትኩረት ከተሰጠባቸው ዘርፎች መካከል ሲሆን፣ በርካታ ወጣቶች የራሳቸውን የምግብ ፍጆታ ከማረጋገጥ አልፈው ወደ ማቀነባበር እና ኢንቨስትመንት ተሸጋግረዋል፡፡ በዓመቱ 54 ሺህ 237 ሊትር ወተት ለማምረት ታቅዶ 61 ሺህ 721 ሊትር ወተት ማምረት ተችሏል፡፡

በንብ ማነብ ዘርፍም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ወጣቶችን ወደ ሥራ እያስገባንበት ያለ ዘርፍ ነው፡፡ በዚህም 358 ቶን ማር ለማምረት ታቅዶ 330 ነጥብ አራት ቶን የማር ምርት ማግኘት ችለናል፡፡

በአጠቃላይ የከተማዋን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ሕዝቡንና አመራሩን ባሳተፈ መልኩ በትኩረት እየተሠራበት ይገኛል፡፡ ዘርፎችን በክላስተር ለማደራጀት 50 ሚሊዮን ብር ተመድቦ የዶሮ ክላስተር እየተገነባ ይገኛል፡፡ የወተት ላምንም ወደ ክላስተር ለማምጣት መሬት ለይተን ለኮንትራክተር በማስረከብ ግንባታ ተጀምሯል፡፡

ዘርፉ የሥራ እና የአመጋገብ ባሕልን መቀየር የሚያስችሉ ውጤቶች እየተገኙ በመሆኑ በሚቀጥሉት ዓመታትም ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን፡፡

አረንጓዴ ዐሻራን በሚመለከት በ2016/17 የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አራት ነጥብ 75 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል 475 ሄክታር መሬትን በችግኝ ለመሸፈን አቅደን እየሠራን እንገኛለን፡፡

የችግኝ ተከላውን ለማከናወን ችግኝ የማፍላት፣ ቦታ የመለየት እና በርካታ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ስንሰራ ቆይተናል፡፡ በ2016 በጀት ዓመት ሶስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ችግኞችን ለማዘጋጀት ታቅዶ ሶስት ነጥብ 25 ሚሊዮን ችግኞችን ለተከላ ማዘጋጀት ችለናል፡፡

ችግኞቹ የተዘጋጁት በከተማዋ በሚገኙ 463 የችግኝ ጣቢያዎች ሲሆን፣ ለተከላ የተዘጋጁት ችግኞች ሁለገብ መኖ፣ ፍራፍሬ፣ ቡና፣ ሀገር በቀል ዛፎች ናቸው፡፡ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ከአካባቢ ጥበቃ በተጨማሪ በጊዜያዊነት እና በቋሚነት ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ፈጥሯል፡፡

ችግኝ መትከል ብቻ ግብ ባለመሆኑ ችግኞች ባለቤት ኑሯቸው ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው በትኩረት እየተሠራ በመሆኑ ጽድቀት መጠናቸውም ከዓመት ወደ ዓመት እየተሻሻለ ነው፡፡

የአካባቢው ማህበረሰብ ችግኝ መትከል የሚያስገኘውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በመረዳት ለ2016/17 የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ፣ ለችግኞች ጥበቃ እና እንክብካቤ እንዲያደርጉ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪ አቀርባለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡-የከተማው ነዋሪ የሚያነሳቸውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ከመፍታት አንጻር የተሠሩ ሥራዎች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ባዩህ፡-** ላለፉት ዓመታት ሕዝቡን ካማረሩ ጉዳዮች አንዱ የመልካም አስተዳደር ችግር ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት እንደ ከተማ በርካታ መድረኮችን አካሂደናል፡፡ አመራሩም ሕዝቡን ያማረረውን ችግር በአጭር ጊዜ ለመፍታት የችሎት መድረክ እንዘረጋለን ብለን በገባነው ቃል መሠረት ከደሴ ከተማ እና ከዙፋን ችሎት ተሞክሮ በመውሰድ በሳምንት አንድ ቀን የሚካሔድ የከንቲባ ችሎት መድረክ ፈጥረናል፡፡

በዚህም ረጅም ጊዜ የቆዩ የፍትህ እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት ችለናል፡፡ ዜጎች ለዘመናት ሲመላለሱበት የነበረውን የመልካም አስተዳደር ጥያቄ የከተማው ነዋሪ፣ አስፈጻሚዎች፣ ባለሙያዎች እና አመራሩ ባሉበት በተጨባጭ ምላሽና ፍትህ በመስጠት የከተማውን ነዋሪ ማስደሰት ተችሏል፡፡ ከንቲባ ችሎት ለሕዝባችን ቃል የገባነው መድረክ በመሆኑ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በከተማዋ የተሟላ ሰላም ቢኖር ከዚህ በላይ ሥራዎችን ማከናወን ይቻል ነበር? በቀጣይስ በከተማዋ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ከማን ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ባዩህ፡-** ከተማዋ በችግር ውስጥ ሆናም የሚታዩና የሚጨበጡ በርካታ ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ጎንደር ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያለባት እና ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ያለው አበርክቶ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

በሰላም እጦቱ የቱሪዝም ዘርፉን ብቻ ወስደን ብናይ በዓመት ግጭት ከመፈጠሩ በፊት በአንድ ዓመት ብቻ ከ160 ሺህ እስከ 200 ሺህ የሚሆኑ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ከተማዋን እንደሚጎበኙና በዚህም ከትኬት ሽያጭ ብቻ ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ በቀጥታ ይገኝ ነበር፡፡ ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሲሰሩ በቢሊዮን የሚቆጠር ሀብት በከተማዋ ኢኮኖሚ ላይ ፈሰስ ይሆን ነበር፡፡

በተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ምክንያት ግን በዘንድሮው ዓመት ማስተናገድ የቻለነው ሁለት ሺህ የሚሆኑ የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን ብቻ ነው፡፡ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችም በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል፡፡ የጸጥታው መደፍረስ ባለፉት ዓመታት ለከተማዋ፣ ለክልልና ለሀገር ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንዲቀንስ ምክንያት ሆኗል፡፡ በሌሎች ዘርፎችም ያሳደረው ተጽእኖ ከፍተኛ ነው፡፡ ብዙ ርቀት መጓዝ እንዳንችል ያደረገ ነው፡፡

በየትኛውም መንገድ ግጭቶች የሚወስዱን የሀገርን ኢኮኖሚ ወደ ማቀጨጭ በመሆኑ በክልልና በከተማ ደረጃ ይህንን ለመቀልበስ ሰፊ ሥራዎችን ስንሰራ ቆይተናል፡፡ በከተማዋ አሁን የተገኘው አንጻራዊ ሰላም መከላከያ ሠራዊት እና የአካባቢው የጸጥታ ኃይል የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ከፍለው ያመጡት ነው፡፡ በሰላሙ መምጣት የሕዝቡም ድርሻ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ አሁን ያገኘነውን አንጻራዊ ሰላም ወደተሟላ ሰላም ለመቀየር የሰላም ካውንስል ተቋቁሞ እየተሠራ ነው፡፡

ግጭት ከችግር ላይ ችግር ከመጨመር ባለፈ የመፍትሔ አካል ሆኖ አያውቅም፤ ስለዚህም ችግሮች በውይይት እና በድርድር እንዲፈቱ መንግሥት፣ የሃይማኖት አባቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን የመወጣት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

እኛ ለዘመናት ያላሸነፍነው እና ወደኋላ የቀረንበትን ድህነት ማሸነፍ የምንችለው የተሟላ ሰላም ስናገኝ በመሆኑ ጫካ የገቡ አካላትም እጃቸውን ለሰላም ሊዘረጉ ይገባል፡፡ ለዘመናት ያላግባቡንን ችግሮች እንደሚፈታ ታምኖበት እንደ ሀገር የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ እየተሠራ ነው፡፡ በዚህም ችግሮችን በንግግርና በውይይት መፍታት ስለሚቻል ሁሉም ችግሩን ወደ ጠረጴዛ በማቅረብ ጎንደር የመልማት እድሏን ያልተጠቀመች ከተማ ስለሆነች ሁላችንም የምንቆጭላት፣ የምንወዳት እና ታሪኳን አውቀን በጋራ የምንገነባት ከተማ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

ሰላም ከማንም አይመጣም፡፡ ሰላም የሚጀምረው ከራስ ነው፡፡ በከተማችን ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በ2017 በጀት ዓመት የተያዙ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ባዩህ፡-** በ2017 በጀት ዓመት ዋናው የትኩረት አቅጣጫችን የሚሆነው የከተማዋን ሰላም ወደ ተሟላ ሰላም መቀየር፣ የከተማዋን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ማነቃቃት፣ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ፣ ከተማዋን ስማርት ሲቲ ማድረግ ነው፡፡

በተለይ ደግሞ አሁን በአዲስ መልክ ወደሥራ እየገባንበት ያለውን የኮሪደር ልማት ሥራ በማጠናከር ከተማዋን ማስዋብ፣ አረንጓዴ መናፈሻ ቦታዎችን መገንባት፣ አገልግሎቶችን ዲጂታላዝድ ማድረግ ላይ ትኩረት ሰጥተን የምንሰራበት ዓመት ነው፡፡

የልማት እና የሰላም ግንባታ ሥራዎችን ብቻችን የምናከናውነው ተግባር አይደለም፤፤ በመሆኑም ሕዝቡ ከጎናችን ሆኖ እንዲያግዘን ጥሪ አቀርባለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን፡፡**

**አቶ ባዩህ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ሀገር በቀል እውቀትን ከዘመናዊው አጣምሮ የሚያሠለጥነው የፋሽን ትምህርት ቤት

**ሰሚራ በርሀ**

የፋሽን ዲዛይን ሕይወትን የጀመረችው ገና በአስራዎቹ እድሜ ላይ ሳለች ነው። በልጅነቷ ለስዕልም የተለየ ፍላጎት ነበራት፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች የምታያቸው የልብስ ዲዛይኖችም ይስቧት ነበር።

ሙዚቃም በልጅነቷ የተሳበችበት ቢሆንም፣ ከሙዚቃ ይልቅ በሙዚቃ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ላይ የምታያቸው ሞዴሎች እና የሙዚቀኞች አልባሳት ዲዛይኖች ወደ ፋሽን ኢንዱስትሪው እንድትሳብ አድርጓታል። ዲዛይነር ማሕሌት አፈወርቅ።

ዲዛይነሯ ለረጅም ጊዜ የቆየ ማፊ ማፊ የተሰኘ የፋሽን ብራንድ ገንብታለች። በማፊ ማፊ የፋሽን ብራንድ የኢትዮጵያን ባሕል ከዘመናዊ ዲዛይን ጋር በማቆራኘት በዓለም አቀፍ መድረክ ሥራዎቿን ስታቀርብም ቆይታለች። ዓለም አቀፍ እውቅናን ማግኘት መቻሏን ገልጻለች።

ዲዛይነር ማሕሌት በሥራው ላይ የ15 ዓመት ልምድን አካብታለች፤ ሥራዋን በጀመረችበት ወቅት ጥራት ያለው የፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤት በሀገሯ አለማግኘቷ ፈተና ሆኖባት እንደነበር ታስታውሳለች። ‹‹እኔ ፋሽን ዲዛይንን ስጀምር ስለ ፋሽን ዲዛይን ራሴን በራሴ ማስተማር ነበረብኝ›› ስትል ትገልጻለች ።

ይህም ጥራት ያለው የፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ መገንባት የረጅም ጊዜ ሕልሟ እንዲሆን አደረገ። የማፊ ማፊ የፋሽን ዲዛይን ብራንድ ሥራ እየሰፋ ሲመጣ በፋብሪካው ውስጥ ለፋሽን ዲዛይን ፍላጎት ላላቸው ወጣቶች ለአጭር ጊዜ የሚቆዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ወደ ሥልጠናውም መግባት እንደ ጀመረች ተናግራለች ።

‹‹ሥልጠና በምንሰጠበት ወቅት ፋሽን እያደገ እንደመጣና ብዙ ፍላጎት፣ ችሎታና አቅም ያላቸው ወጣቶች ማየት ቻልኩ›› የምትለው ዲዛይነር ማሕሌት፣ ትምህርት ቤቱ በሀገራችን እና በሌላው ዓለም ዘንድ ያለውን የእውቀት ክፍተት ለመሙላት ማለሙን ገልጻለች።

እሷ እንዳለችው፤ የፋሽን ኢንዱስትሪ በሌላው ዓለም ትኩረት ተሰጥቶት በቢሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ የሚንቀሳቀስበት እና ውበት ብቻ ሳይሆን ታሪክን ጭምር መናገር የሚችል ኢንዱስትሪ መሆን ችሏል።




በሀገሪቱ ይህን ዘርፍ ለማሳደግ ጥራት ያለው የፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤት ያስፈልጋል የሚል ሕልምም የነበራት ዲዛይነሯ፣ ይህ ሕልሟ እውን ሆኖ የማፊ ፋሽን አካዳሚ እና ቤተሙከራ በአዲስ አበባ እውን መሆኑን አስታውቃለች።

የአካዳሚውና ቤተሙከራው እውን መሆንን አስመልክቶ በተሰጠ መግለጫ ላይ እንደተጠቆመው፣ አካዳሚው በአፍሪካ የተሳካ ዓለማቀፋዊ ብራንዶችን መፍጠር የሚችሉ እና በከፍተኛ ሁኔታ የሠለጠኑ የፋሽን ባለሙያዎች የሚሠለጥኑበት ነው።

አካዳሚው አዳዲስ የፋሽን ዲዛይን አሠራሮችን ስኬታማ ማድረግ ከሚያስችሉ የሥራ ፈጠራ ክህሎቶች ጋር በማጣመር የፋሽን ትምህርት ይሰጣል። ሥርዓተ ትምህርቱም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ የፋሽን አማካሪዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው። ‹‹15 ዓመት ከቆየሁበት የፋሽን ኢንዱስትሪ እንዲሁም በሀገሪቱም ሆነ በአፍሪካ ያሉትን የዘርፉን ክፍተቶች በመለየት የተዘጋጀ ነው›› ብላለች።

ትምህርት ቤቱ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ዘመናዊ የመማሪያ ማሽኖችን እና በኢትዮጵያ ውስጥ ብቁ የሆኑ የፋሽን አስተማሪዎችን ማግኘት አስቸጋሪ እንደነበር ጠቅሳ፣ ይህን ክፍተት ለመሙላት አካዳሚው ከኢትዮጵያ የጣሊያን ኤምባሲ ፣ በጣሊያን ሀገር ከሚገኘው ዩኒቨርሳል አርት አካዳሚ ጋር በመተባበር መመሥረቱን ጠቁማለች ።

በመግለጫው ላይ በኢትዮጵያ የጣሊያን አምባሳደር አጎስቲኖ ፓሌዜ፣ የዩኒቨርሳል አርት አካዳሚ የጣሊያን ተወካይ እና የተባበሩት መንግሥታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት (UNIDO) ተወካዮች ተገኝተዋል።

ዲዛይነር ማሕሌት እንዳብራራችው፤ ትምህርት ቤቱ ከፋሽን ዲዛይን እውቀት በዘለለ ሠልጣኞች ያላቸውን አቅም በመጠቀም በፋሽን ኢንዱስትሪ ገቢ ማግኘት እና ውጤታማ መሆን የሚችሉባቸው ሀሳቦችም ተካተዋል። ሥልጠናው ሠልጣኞች ከፋሽን ዲዛይን፣ ከፋሽን ቢዝነስ፣ ከፋሽን ፎቶግራፍ፣ ከፋሽን ስታይሊንግ፣ ከፋሽን ቴክኖሎጂ እና ከመሳሰሉት በመረጡት መስክ ሥልጠናውን እንዲከታተሉ ተደርጎ መዘጋጀቱንም ጠቁማለች።

በመግለጫው ላይ እንደተጠቆመው፤ የትምህርት ሥርዓቱ የሀገር በቀል ባሕላዊ እውቀትን ከዓለም አቀፉ ጋር በማስተሳሰር ተዘጋጅቷል። ትምህርቱ የሚሰጠው በጣሊያን ባለሙያዎች እንዲሁም ዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ባላቸው ባለሙያዎች ሲሆን፣ ዲዛይነሮች፣ የቢዝነስ አማካሪዎች፣ የፎቶግራፍ ባለሙያዎች ይሳተፉበታል። ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች ወደጣሊያን ሀገር በመሄድ የተሻለ ሥልጠና እንዲያገኙ እንዲሁም በአፍሪካ እና በኤሽያ በሚደረጉ ዓለም አቀፍ የልምድ ልውውጦች ላይም እንዲሳተፉ ይደረጋል።

የተባበሩት መንግሥታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት (UNIDO) ተወካይ እንደገለጹት፤ የሀገር ውስጥ እውቀት እና ዕድሎችን ከዓለም አቀፉ ጋር ለማስተሳሰር ይሠራል፤ ድርጅቱ ቴክኒካል የሆኑ የመሣሪያ ድጋፎችን በማድረግ ያግዛል።

የጣሊያኑ ዩኒቨርሳል አርት አካዳሚ ተወካይ በበኩላቸው የፋሽን ኢንዱስትሪ ለጣሊያን ዋነኛ ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ ከዚህ ልምድ ልትወስድ ይገባል ብለዋል።

አካዳሚው ሠልጣኞችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለው የፋሽን ኢንዱስትሪው ጋር ማስተዋወቅ ያስችላል፤ ኢትዮጵያውያን የፋሽን ዲዛይነር ሠልጣኞች በሌላው ዓለም ላይ በመሥራት እና አቅማቸውን በማሳየት ለውጥ ማምጣት የሚችሉበትን ዕድልም ያመቻቻል።

ትምህርቱ የሦስት፣ የስድስት ወራት እና የአንድ ዓመት በሚል እንደሚሰጥ የተጠቆመ ሲሆን፣ በአንድ ጊዜ እስከ 120 ተማሪዎች መያዝ እንደሚችልም ተገልጿል። የትምህርት ቤቱ የፋሽን ፈጠራ ላቦራቶሪ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሲሆን፣ ተማሪዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲመራመሩና ለወደፊቱ የዘርፉ ኢንዱስትሪ ሥራ እንዲያዘጋጁ ያስችላል ።

ተማሪዎች ሥልጠናቸውን ጨርሰው ሲመረቁ የራሳቸውን ቢዝነስ ማቋቋም፣ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በሥራ ቅጥር በመሥራት ለውጥ ማምጣት እንዲችሉ፣ በውጭ ሀገር ተጨማሪ ትምህርቶችን ለመከታተል እንዲሁም ሽርክና መፍጠር አልያም በዓለም አቀፍ ደረጃ ስኬታማ እንዲሆኑ በማድረግ በኩልም የምክር አገልግሎት እንደሚሰጣቸውም ተጠቁሟል።

ትምህርት ቤቱ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽነቱን የማስፋት እቅድ እንዳለው ጠቅሳ፣ ሥልጠናውን ለመውሰድ ወደ አካዳሚው የሚመጡ ሠልጣኞችን ለመቀበል አካዳሚው የራሱ የሆነ ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሉትም ዲዛይነር ማሕሌት አስታውቃለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የቅድመ ቁጣ አገልግሎት ሰጪዎች

**ዋሰልኝ አየለ**

በብዙ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ አገልግሎቱን የሚሰጡ ሠራተኞች ሲቆጡና ሲያመናጭቁ ማየት የተለመደ ነው። ምንም እንኳን ግልምጫና ስድብ ትክክል ባይሆንም፤ ቢያንስ ግን ተገልጋዩ ያለአግባብ ልስተናገድ ብሎ ካስቸገረ በኋላ አይሻልም? እንዴት የዱቤ ይቆጣሉ? መጀመሪያ ልቆጣህና የአንተ ጥፋት በኋላ ይደርሳል የሚሉ ነው እኮ የሚመስለው!

ችግሩ ያለው የፀጥታና የሥነ ምግባር ኃላፊነት ያለባቸው ላይ ጭምር ነው። ለምሳሌ፤ አንዳንድ ፖሊሶች አስቀድመው ይቆጣሉ። ባለጉዳዩ ሥነ ሥርዓት ያለው እና በሠለጠነ መንገድ የሚያናግር ከሆነ ከቁጣ መጀመር ምን ይሉታል?

ይሄ ማለት ግን ተገልጋይ ላይ ችግር የለም ማለት አይደለም። አናዳጅ ብቻ ሳይሆን ከማናደድ አልፎ ሊያስቁ የሚችሉ ሰዎች አሉ። ከዚህ በፊት በሌላ ጽሑፍ የተጠቀምኩት አንድ ገጠመኝ ልጥቀስ።

ከዓመታት በፊት በአዋሽ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ውስጥ ያስተዋልኩት ነው። ደንበኞች የሚስተናገዱት በትኬት ቁጥር ነው። የትኬቱ ቁጥር የተጠራ ተረኛ ወደተጠራበት መስኮት ሄዶ ይስተናገዳል። አንድ ተገልጋይ የያዘው ትኬት ቁጥር ሳይጠራ ተነሳና ሠራተኛ ወደሌለው ባዶ መስኮት ሄደ። የሰውየው ወደዚያ መሄድ ግራ የገባው ከባዶው መስኮት ጎን ያለው የባንኩ ሠራተኛ ‹‹ና›› አለው። ተገልጋዩም ‹‹ና›› ወዳለው የባንክ ሠራተኛ ሄደና የሞላውን ቅጽ ለባንክ ሠራተኛው (ቴለር) ለመስጠት እጁን ሰነዘረ።፡ ሠራተኛውም ‹‹አይ! ምናልባት ብር ለመዘርዘር ወይም ለሌላ ቀላል ጉዳይ መስሎኝ ነው፤ ለመገልገል ከሆነ ቁጥርህ ሲጠራ ነው›› አለው። ደንበኛው ‹‹አስተናግደኝ!›› አለ። የባንኩ ሠራተኛ ትኬቱን ተቀብሎ ሲያይ ገና ብዙ ይቀረዋል። ‹‹አይቻልም›› ብሎ ከለከለው። ደንበኛው ‹‹ታዲያ ለምን ጠራሽኝ?›› ብሎ ተቆጣ። የባንክ ሠራተኛውም በትዕግስት ማስረዳት ጀመረ። ‹‹የጠራሁህ ለሌላ ጉዳይ መስሎኝ ነው፤ በዚያ ላይ ሰው በሌለው መስኮት ነው የሄድክ፤ እዚያ ማንም ሊያስተናግድህ አይችልም፤ ባልጠራህ ባዶ መስኮት ጋ ምን ልትሠራ ነበር?›› አለው። ደንበኛው ጭራሽ ባሰበት።

ለመገልገል የገባው ደንበኛው ሙሉ በሙሉ ጥፋቱ የራሱ ሆኖ ሳለ ቁጣውም የራሱ ሆነ። ጭራሽ እንዲያውም የተቋማት ሠራተኞችን ዝርክርክነት ሁሉ እየጠቀሰ ይሳደብ ጀመር። ልክ እሱ የሠለጠነ ይመስል እንደ ሀገር ያለው አሠራር ያልሠለጠነ መሆኑን በቁጭት ይናገራል።

አንዳንዱ ንዴቱን ቻል አድርጎ ይስቃል፤ አንዳንዱም እየታዘበ ዝም ይላል። እርግጥ ነው በተቋማት ውስጥ ብዙ የተዝረከረከ አሠራር አለ፤ ግን ይሄ ሰውየ እነዚህ ሰዎች የመተቸት ሞራል አለው? ሠራተኛው ብቻ እንጂ ተገልጋዩ ሥነ ሥርዓት መያዝ የለበትም ማለት ነው? ይሄ ሰውየ እኮ የዚያን ሁሉ ተገልጋይ ሰዓት እያባከነ ነው፤ በዚያ ላይ የአሠራር ደንብም እየጣሰ ነው። የትኬት ቁጥር ያስፈለገው እኮ መተራመስ እንዳይኖርና ሥራውን የተቀላጠፈ ለማድረግ ነው፤ አሁን ይሄን ሰውየ ምን ይሉታል እንግዲህ?

በኋላ የባንክ ሠራተኛውም ትዕግስቱ እያለቀ መጣ። ወደ አላስፈላጊ ክርክር ውስጥ ገቡ። የዚህን ጊዜ ሌሎች ተገልጋዮች ጣልቃ እየገቡ መገላገል ጀመሩ። የባንክ ሠራተኛው ዝም በል ሲባል ዝም አለ። ተገልጋዩ ግን ቁጣውን ያወርደው ጀመር። በኋላ የባንክ ሠራተኛው ጭራሽ እየሳቀ ያበሸቀው ጀመር። በነገራችን ላይ ነገሮችን ንቆ መተው ትልቅ ጥቅም አለው። ያንን ተሳዳቢውን በጣም ነው የሚያናድደው። ሠራተኛው ሥራውን መሥራት ጀመረ። ባለጉዳዩ ሲለፈልፍ ቆይቶ ትቶት ወጣ። ግልግል ሆነ ማለት ነው!

እንግዲህ አንዳንዱ ሰው እንዲህ ነው። የባንክ ሠራተኛው ጨዋ ባይሆን ኖሮ፣ ነገሩን ንቆ ባይተወው ኖሮ እነዚህ ሰዎች እስከመደባደብ ይደርሱ ነበር። ሲደባደቡ ያየ ሰው ጥፋቱ የማን እንደሆነ ካላወቀ በሁለቱም ይፈርድ ነበር። አንዳንድ ሰዎች በጣም ግርም ይላሉ። ከይቅርታ ይልቅ ስድብ ይገዛቸዋል። ይቅርታ ሲባሉ የተፈሩ ይመስላቸዋል።

ምንም እንኳን ችግሩ ያለው ከሁለቱም (ከአገልጋይም ከተገልጋይም) ቢሆንም ታጋሽነትና የሠለጠነ አሠራር የሚጠበቀው ግን ከአገልግሎት ሰጪዎች ነው። ምክንያቱም ኃላፊነት ላይ የተቀመጡት የተሻለ ብቃት ኖሯቸው ነው። ተወዳድረው ነው። ሀገራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት ነው። ሀገራዊ ኃላፊነት ሲባል የግድ በከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን ብቻ መሆን የለበትም። የአንድ ተቋም የጥበቃ ሠራተኛ ለዚያ ሥራ ኃላፊ ነው። ሥራውም ሀገራዊ ሥራ ነው። ሀገረ መንግሥት ሲባል የግድ ዳር ድንበሩ ብቻ አይደለም። የአሠራር መዋቅሩ ጭምር ነው። ስለዚህ አንድ ሀገር ሠለጠነች የሚባለው የአሠራር ሂደቱ የሠለጠነ ሲሆን ነው።

ሰዎች ሥነ ምግባርን መማር ያለባቸው በኃላፊነት ላይ ካሉ ሰዎች ነው። በአገራችን የምናየው ነገር ግን በቁጣ መጀመር ነው። ከአንድ ሳምንት በፊት ከግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር በተያያዘ ጉዳይ አንድ የቀበሌ አገልግሎት ተቋም ሄጄ ነበር። እርግጥ ነው በግሌ ለማማረር የሚያበቃ መጉላላት አላጋጠመኝም። ያስተዋልኩት ችግርም የዚያ ቢሮ ሠራተኞች የተለየ ችግር ሳይሆን እንደ ሀገር የሠለጠነ አሠራር ባለመስረጹ ያጋጠመ ነው።

የተሰጠው ቅጽ ግልጽነት የለውም። መጠይቆቹ አሻሚ ናቸው። ቅጹን የሚሞሉ ሰዎች ‹‹እዚህ ላይ ምንድነው የሚሞላ?›› እያሉ አገልግሎት ሰጪዎችን ለመጠየቅ ይገደዳሉ። ይህኔ ነበር በሁለቱም በኩል መሰለቻቸት የሚታየው። አገልግሎት ሰጪዎቹ ሥራ እያቋረጡ ያን ሁሉ ሰው ማስረዳት ይሰለቻቸዋል። ተገልጋዮች ደግሞ በግምት ቢሞሉት በኋላ ‹‹ትክክል አይደላችሁም›› ሊባሉ ነው።

በሌላው በጣም በተደጋጋሚ የማስተውለው ችግር ግን የትኛው ጉዳይ የት እንደሆነ አለማወቅ ነው። አገልግሎት ሰጪዎች ሲጠየቁ ባለጉዳዩ የዚያ ቢሮ ነዋሪ የሆነ ይመስል ‹‹እንዴት ይሄን አታውቅም?›› የሚል ድምጸት ባለው ቁጣ ‹‹ማነው እዚህ ነው ያለህ?›› ብለው ይቆጣሉ። ባለጉዳዩ የጠየቀውን ቢሮ በትህትና ከመጠቆም ይልቅ እነርሱ ጋ አለመሆኑን ብቻ በቁጣ የሚናገሩ አሉ። ምንም እንኳን እንዲህ የሚያደርጉት በጣም ጥቂቶች ቢሆኑም በእነዚህ ጥቂቶች ምክንያት ግን ተቋሙ ይወቀሳል። ተቋሙ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ሀገራዊ አገልግሎቱም ይወቀሳል።

በሥራ ጫና ምክንያት መሰላቸት እንደሚኖር ይታመናል። አንዳንዶቹ ግን በሚያስቅ ሁኔታ ወንበራቸው ላይ ጀርባቸውን አስደግፈው እያሽከረከሩ ስልካቸውን በመጎርጎር ላይ ሆነው ነው ባለጉዳይ ሲመጣ በቁጣ የሚጀምሩት። ታዲያ እነዚህ አያናድዱም?

ቢቻል ሁሉንም በትዕግስትና በትህትና ማስተናገድ፤ ሰው ናችሁና በሥራ ጫና ምክንያት መዋከብ ቢኖርም ቢያንስ ግን በሠለጠነ መንገድ የሚስተናገደውን ሁሉ ባታደነባብሩ። የቅድመ ቁጣ አገልግሎት አትስጡ!

# ጀርመን

# በአፍሪካ ቀንድ ያላት ትኩረት ዕድሎች ፣ ስጋቶችና ቀጣይ አቅጣጫዎች

**በፍቃዱ ቦጋስ (ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት)**

**መግቢያ፤**

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የአፍሪካ ቀንድ የተለያዩ ዓለም አቀፍ እና ቀጠናዊ ኃያል ሀገራት (global and regional powers) ትኩረትን ይበልጥ እየሳበ ይገኛል:: ለአፍሪካ ቀንድ ተጨማሪ ትኩረት መስጠት ከጀመሩ ሀገራት መካከል አንደኛዋ ጀርመን ናት::

ጀርመን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ እ.ኤ.አ በጁን 2023 ላይ ሾማለች:: ልዩ መልዕክተኛው ኢትዮጵያን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራትን እንዲሁም በአፍሪካ ቀንድ ዙሪያ የሚሰሩ እንደ የኤምሬት ፖሊሲ ማዕከል (Emirates Policy Centre) ያሉትን ጎብኝተዋል፤ የአውሮፓ ህብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛዋ ለጀርመን ፓርላማ አባላት እ.ኤ.አ ፌብሯሪ 21፣ 2024 ማብራሪያ እንዲሰጡ ተደርጓል::

የጀርመን ጦር በአውሮፓ ህብረት ስር በሶማሊያ ባህር ዳርቻ ፀረ-ባህር ላይ ውንብድና ተሳትፎ ያደርጋል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ እንደ ትልቅ ርምጃ ሊታይ የሚችለው በጀርመን ፓርላማ ሁለተኛ ባለ ብዙ መቀመጫ የሆነው የክርስትያን ዲሞክራቲክና ክርስቲያን ሶሻል ጥምረት (CDU/CSU) “ጠንካራ የጀርመን ተሳትፎ በአፍሪካ ቀንድና በኤደን ባህረ ሰላጤ” (A stronger German involvement in the Horn of Africa and the Gulf of Aden) በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በጁን 6፣ 2024 ረቂቅ የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ማቅረቡና ፓርላማውም ረቂቁን ከተመለከተ በኋላ ለውጭ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ መምራቱ ነው::

ሰነዱ የአፍሪካ ቀንድ ከፍተኛ ጂኦ-ፖለቲካዊ እና ጂኦ-ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ቀጠና ቢሆንም በጀርመን መንግሥት በኩል “ስትራቴጂካዊ ቸልተኛነት” እንዳለ በመተቸት ይህ ሁኔታ መቀየር እንዳለበት ያስቀምጣል:: በተለይም ተጨማሪ ዲፕሎማቲክ እና ወታደራዊ ባለሙያዎችን ወደ ቀጠናው መላክ እንደሚያስፈልግ ተመላክቷል::

በአጠቃላይ በንግድ፣ ርዳታና ድጋፎች ላይ የሚያተኩረው የጀርመን-አፍሪካ ቀንድ ግንኙነት ለፀጥታና ደህንነት ጉዳዮች ከፍተኛ ትኩረት ወደ መስጠት እየተሸጋገረ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል:: ስለዚህ ረቂቅ ውሳኔ ሃሳቡ ሆነ አጠቃላይ የጀርመን ከፍ ያለ የአፍሪካ ቀንድ ትኩረት መነሻ ምክንያቶች ምንድናቸው ? ከኢትዮጵያ አንጻር ምን ስጋቶችንና ዕድሎችን ይዟል እንዲሁም ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ምንድናቸው ? የሚለውን መዳሰስ አስፈላጊ ነው::

**መነሻ ምክንያቶች፤**

ጀርመን ለአፍሪካ ቀንድ የምትሰጠው ትኩረት እንዲጨምር የሚያደርጉ ብዙ መነሻ ምክንያቶች አሏት:: ከእነዚህም መካከል በአፍሪካ ቀንድ ያለው ያለመረጋጋት ሁኔታ ተጠቃሽ ነው። በተለይም በሶማሊያ የቀጠለው አለመረጋጋትና ፀረ-አልሸባብ ዘመቻው በተፈለገው ልክ ስኬታማ ያለመሆን ፤ የሱዳን እርስ በእርስ ጦርነት ለስደተኞች ቁጥር መጨመር እንዲሁም ለሽብርተኛነትና የባህር ላይ ውንብድና መጠናከር አስተዋጽኦ ማድረግ ለጀርመንም ሆነ ለአውሮፓ የደህንነት ስጋት ይደቅናል የሚለው የመጀመሪያው ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል::

ከዚህ ጋር በተያያዘ መነሳት ያለበት ጉዳይ ከአውሮፓ ወጪና ገቢ ንግድ 20 ከመቶ በላይ የሚሆነው የሚዘዋወረው በአፍሪካ ቀንድ ዳርቻ የውሃ አካላት መሆኑ ነው:: ሌላኛው ምክንያት የተለያዩ ሀገራት በአፍሪካ ቀንድ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ወታደራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ሚናቸው እየጎላ መምጣቱ ነው:: በመሆኑም ጀርመን ስትራቴጂያዊ ጥቅሟን ለማስከበርና እንደ ራሺያ፣ ቻይና፣ ቱርክ እና ኢራን ያሉ ሀገራትን ተጽዕኖ ለመቋቋም በራሷም ሆነ በአውሮፓ ህብረት ጥላ ስር እንቅስቃሴዎችን ማድረጓ ተጠባቂ ነው::

**የግሎባል ጌትዌይ ኢንሽቲብ አካል የሆኑ ፕሮጀክቶች በሀገራችን ውስጥም ሆነ በቀጠናው ከታቀዱ የመሠረተ-ልማት ሥራዎች ጋር ሊናበቡ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች በማጤን የተጠናከረውን የጀርመን ፍላጎት እንደ አንድ ዕድል መጠቀም ይቻላል**

በሦስተኛነት ሊነሳ የሚችለው ምክንያት ጀርመን በአፍሪካ ቀንድ እየተስተዋሉ ካሉ ለውጦችና አዳዲስ ክስተቶች ተጠቃሚ የመሆን ፍላጎት ነው:: በዚህ ረገድ የቀጠናው ሀገራት ትላልቅና ድንበር ተሻጋሪ መሠረተ-ልማቶች እየጀመሩና እያቀዱ መሆኑ፤ በኢትዮጵያ ያለው ከፍተኛና ለብዙ ሀገራት ሊቀርብ የሚችል የታዳሽ ኃይል አቅምና ልማት፤ በሶማሌላንድ፣ በደቡብ ሱዳን እንዲሁም በኢትዮጵያ ለተለያዩ ኢንቨስትሜንቶች የተሻለ ምቹ ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑ ተጠቃሽ ናቸው::

በጀርመን በኩል እነዚህን ዕድሎች ከአውሮፓ ህብረት ግሎባል ጌትዌይ ኢንሼቲቭ (Global Gateway Initiative) ጋር በማስተሳሰር የማስኬድና የቻይናውን ቤልት ኤንድ ሮድ ኢንሼቲቭን (Belt and Road Initiative) በአፍሪካ ቀንድ መቀናቀን የሚለው ትኩረት የተሰጠው ይመስላል::

**አስቻይ ዕድሎች፤**

ጀርመን ለአፍሪካ ቀንድ የምትሰጠው ትኩረት ከፍ ከማለቱ ጋር በተያያዘ ከተነሱት ስጋቶች ጎን ለጎን ዕድሎችም አሉ:: አንደኛ በልዩ መልዕክተኛው የኢትዮጵያ ጉብኝት ወቅት ሆነ በረቂቅ ሰነዱ ኢትዮጵያ ለቀጠናው ሰላም ስታበርክት የነበረውና ልታበረክት የምትችለውን አስተዋጽኦ በግልጽ ዕውቅና የተሰጠው መሆኑና በቀጣይም ሀገራችን ይህን ሚና በተሻለ እንድትወጣ ጀርመን ድጋፎችን እንደምታደርግ መመላከቱ በበጎ ጎኑ ሊነሳ የሚችል ነው::

ጀርመን ከሌሎች ምዕራባዊያን በተለየ ሁኔታ የኢትዮጵያ ወዳጅ ከሆነችው ቻይና ጋር በአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች አብሮ መሥራት እንዳለባት መቀመጡ፤ ሀገሪቱ በአፍሪካ ቀንድ ያላትን ጂኦ-ፖለቲካዊ ፍላጎት ለማሳካት አብሮ መሥራት እንዳለባት ከተለዩ አንዳንድ ሀገራት ጋር ኢትዮጵያ ጥሩ ግንኙነት ያላት መሆኑና በተለይም ከተባበሩት አረብ ኤምሬትስ (UAE) ጋር ካለን ስትራቴጂካዊ ወዳጅነት አንጻር ጀርመንን በሱዳን እና በሶማሌላንድ ላሉን ፍላጎቶች በጎናችን የምናሰልፍበት መልካም ዕድል ሊኖር ይችላል::

በሶስተኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ጀርመን በራሷና በአውሮፓ ህብረት ስር የምታከናውናቸው እንቅስቃሴዎች ለብሔራዊ ጥቅማችን አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ መሆኑ ነው:: በዚህ ረገድ የግሎባል ጌትዋይ ኢንሽቲቭ አካል የሆኑ ፕሮጀክቶች በሀገራችን ውስጥም ሆነ በቀጠናው ከታቀዱ የመሠረተ-ልማት ሥራዎች ጋር ሊናበቡ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች በማጤን የተጠናከረውን የጀርመን ፍላጎት እንደ አንድ ዕድል መጠቀም ይቻላል:: በተጨማሪ በአፍሪካ ቀንድ ባህር ዳርቻ የባህር ላይ ውንብድናን መከላከል አንዱ የጀርመን ትኩረት ጉዳይ ተደርጎ መቀመጡ በጉዳዩ አብሮ የመሥራት ዕድል ከመስጠት ባሻገር ችግሩ በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊና የደህንነት ተጽዕኖ እንዲቀንስ የጀርመን የተጠናከረ እንቅስቃሴ የራሱን አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል::

**ተጠባቂ ስጋቶች፤**

ከጀርመን የጨመረ የአፍሪካ ቀንድ ትኩረት ጋር በተያያዘ ሊነሱ የሚችሉ ስጋቶች አሉ:: አንደኛ ብዙም ጠንካራ ጂኦ-ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን አድርጋ የማታውቀው ጀርመን በዚህ ደረጃ ለአፍሪካ ቀንድ ትኩረት መስጠቷ የቀጠናውን ጂኦ-ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ከማሳየት ባሻገር በኃያላንና ሌሎች ሀገራት መካከል ፉክክር እያየለ መምጣቱን የሚያሳይ ነው:: ይህም በቀጠናው ሀገራት መካከል ከኃያላን ያለን ወዳጅነት መነሻ በማድረግ ክፍፍልን ሊያሰፋ፣ ልዩነቶች እንዲባባሱ ብሎም የቀጠናው ሀገራት ቀጥታ በማይመለከታቸው የሌሎች አጀንዳዎች እንዲሳቡ የራሱን አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል::

ሁለተኛ በተለይም በረቂቅ ሰነዱ ሩስያን እና ኢራንን በስጋትነት በመፈረጅ ሀገራቱ በቀጠናው ያላቸውን እንቅስቃሴ መቃወም ከዋነኛ የጀርመን የአፍሪካ ቀንድ ትኩረቶቹ አንዱ መሆን እንዳለበት መቀመጡ እነዚህ ሁለቱ ሀገራት አፀፋዊ ርምጃ እንዲወስዱ በማድረግ የኢትዮጵያን ጥቅም ሊጎዳ ይችላል:: ለምሳሌ ሩስያ ለሱዳን ጦር ድጋፎችን ብታጠናክር እና በፖርት ሱዳን አካባቢ ጦር ሰፈር ብትገነባ፣ በተመሳሳይ ሁለቱ ሀገራት ለኤርትራ ወታደራዊና ሌሎች ድጋፎች ካጠናከሩ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ሊደቅን ይችላል::

በሶስተኛነት ሊነሳ የሚችለው ከቀጣይ ትብብርና ዲፕሎማሲ አንጻር ከጀርመን ጋር ያለው ግንኙነት ክፍተቶች ሊፈጠሩ የሚችሉበት አዝማሚያ መኖሩ ነው:: ለምሳሌ በረቂቅ ሰነዱ የሶማሊያን መንግሥት ማጠናከርና አብሮ መሥራት እንደ አንድ ጉዳይ የተቀመጠ ሲሆን ይህም አሁን ካለው ቀጠናዊ ሁኔታ አንጻር ለፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ የፀረ ኢትዮጵያና ሶማሌላንድ እንቅስቃሴ ተጨማሪ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ አቅም ሊሆን ይችላል:: በተጨማሪ ረቂቅ ሰነዱ የልማት ትብብርና ድጋፎችን ከጂኦ-ፖለቲካዊ ፍላጎት ጋር ማስተሳሰር እንደሚያስፈልግ ማስመሩ ኢትዮጵያ ከጀርመን ጋር ያላትን ትብብር ሊያወሳስብ፣ አንዳንድ ድጋፎች እንዲቀንሱ ሊያደርግ የሚችል መሆኑ ተጠቃሽ ነው::

**መፍትሔዎች፤**

ከሚታዩ ስጋቶች እንዲሁም ከመፃኢ ዕድሎች አንጻር ኢትዮጵያ ምን ማድረግ አለባት የሚለው ቁልፍ ጥያቄ ነው:: በመሆኑም እየጨመረ ከመጣው የጀርመን የአፍሪካ ቀንድ ትኩረት አንጻር የስጋቶችን ተጽዕኖ ለመቀነስ እንዲሁም ዕድሎችን በተሻለ ለመጠቀም በኢትዮጵያ በኩል የተለያዩ ተግባራት መከናወን እንዳለባቸው ማስቀመጥ ይቻላል::

አንደኛ በቀጣናው የኢትዮጵያን ስትራቴጂካዊ ተፈላጊነት ይበልጥ የሚጨምረውንና ከሶማሌላንድ ጋር የተደረሰውን የመግባቢያ ስምምነት ወደ ተግባር ማሸጋገርና ለሶማሌላንድ የአጋርነት ዕውቅና በመስጠት ጭምር ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን መጀመር (ለምሳሌ ባህር ኃይላችንን ማስፈር) ቀዳሚ ርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: በዚህም ሶማሌላንድ ከሌሎች የተሻለ ቁመናና እምቅ አቅም ያላት ብሎም ለጀርመን ሆነ ለአውሮፓ ህብረት አስተማማኝ ወዳጅና አጋር ልትሆን የምትችል እንደሆነች እንዲሁም ኢትዮጵያ ባህር ዳርቻውን ጨምሮ የቀጠናውን ሰላምና ደህንነት ይበልጥ ለማረጋገጥ አቅሙም ዝግጁነቱም ያላት መሆኑን ማጉላት ይቻላል::

ሁለተኛ ከጀርመን ጋር ያለንን ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር ያስፈልጋል:: ለምሳሌ በመሪዎች ደረጃ ኢትዮጵያ የጀርመንን ጂኦ-ፖለቲካዊ ፍላጎት እንደምትረዳና በጋራ ጉዳዮች አብሮ ለመሥራት ሙሉ ዝግጁነት እንዳለ ማሳወቅ፣ ኢትዮጵያ ለቀጠናው የምታበረክተውን እንደ ስኬታማ ፀረ-ሽብር ሥራዎቻችን ያሉ ተግባራትን አጉልቶ ማስረዳት፣ ቁልፍ ሀገራዊ ተቋማት (በተለይም ፌዴራል ፖሊስ፣ ብሔራዊ መረጃ፣ መከላከያ) ከጀርመን አቻዎቻቸው በጋራ ጉዳዮች ዙሪያ የትብብር ዕድሎችን መቃኘት እንዲጀምሩና እንዲያጠናክሩ ማድረግ፤ ቀጠናዊ ስትራቴጂያችንን (ማለትም ኢጋድን በተመለከተ፣ ድንበር ተሻጋሪ መሠረተ-ልማቶችን በተመለከተ፣ ቀጠናዊ ሰላምና ደህንነትን በተመለከተ ያለንን ስትራቴጂ) ይበልጥ አጉልቶ ማሳወቅ በዲፕሎማሲ ረገድ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው::

በአጠቃላይ ጀርመን ለአፍሪካ ቀንድ የምትሰጠው ትኩረት ቀጣናውም ሆነ የዓለም ሁኔታ እየተለዋወጠ መምጣት ጋር የተገናኘ ሲሆን ሁኔታው ይዟቸው የሚመጣቸውን ስጋቶች ለመቀነስና ዕድሎችን ደግሞ ለመጠቀም የተጠናከረና የተቀናጀ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል:: ለዚህም መነሻ ግብዓት የሚሆኑ ብዙ መደላድሎች ያሉ መሆኑ ሊጠቀስ ይገባል::

# ስፖርት





# እግር ኳስ የማይቀዘቅዝባት ከተማ- አርባ ምንጭ

**ብርሃን ፈይሳ**

በኢትዮጵያ እግር ኳስ በርካታ ተጫዋቾችን በማፍራት ተጠቃሽ ከሆኑ ስፍራዎች መካከል አርባ ምንጭ ከተማ እና አካባቢው አንዱ ነው:: ከዓመት ዓመት እግር ኳስ እንደተሟሟቀ የሚካሄድባት አርባ ምንጭ ያፈራቻቸው ከ85 በላይ ተጫዋቾች በዚህ ወቅት ብቻ ከብሔራዊ ሊግ እስከ ፕሪምየር ሊግ ባሉት የውድድር እርከኖች ላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ:: በብሔራዊ ቡድን ደረጃም ከአርባ ምንጭ የተገኙ በርካታ ተጫዋቾች ሃገራቸውን የሚወክሉ ሲሆን፤ ይህንኑ በአደረጃጀትና በውጤታማነት አጠናክሮ ለመቀጠል የከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽሕፈት ቤት በትኩረት እየሠራ ይገኛል::

የከተማዋ መለያ የሆነው አርባ ምንጭ ከተማ(አዞዎቹ) ከኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ በወረድ ዓመት ራሱን አጠናክሮ በከፍተኛ ሊጉ ብልጫ በማስመዝገብ ወደ ተፎካካሪነቱ መመለስ መቻሉ ይታወቃል:: ይህንንም ተከትሎ ክለቡ በገቢ ተጠናክሮ ራሱን እንዲችል ለማድረግም ሃገር አቀፍ የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብር መዘጋጀቱን የአርባ ምንጭ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ጌታ ሸታ ለአዲስ ዘመን ተናግረዋል:: ሃብት በማሰባሰብ ሂደቱም ሕዝባዊ የሩጫ ውድድር፣ የአደባባይ የቦክስና የቴኳንዶ ውድድሮች እንዲሁም ከተማዋ ያፈራቻቸው አንጋፋ ተጫዋቾችን የሚያሰባስብ ዝግጅት ለማከናወን ታቅዷል::

በመላው ኢትዮጵያ ክለቦች ውስጥ የሚገኙት እነዚህ ተጫዋቾችም የውድድር ዓመቱን መጠናቀቅ ተከትሎ የክረምቱን ወቅት የሚያሳልፉት በከተማዋ እንደመሆኑ የተለያዩ ውድድሮች ይዘጋጃሉ:: ልማት ካፕ እና ሰመር ካፕ በሚል ውድድሮች እየተካሄዱ ሲሆን፤ በዚህም ሂደት ስፖርቱን ከማሳደግ ባለፈ ተተኪ የእግር ኳስ ተጫዋቾችን በማፍራት እንዲሁም አዳዲስ ተጫዋቾች በክለቦች ዓይን እንዲገቡ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ጥቅም አላቸው:: ዘንድሮ 10ኛ ዓመቱን ያስቆጠረው ልማት ካፕ በዚህ ዓመት በድንገተኛ ሁኔታ ያለፈውን ወጣት ተጫዋች አለልኝ አዘነን በመዘከርም ነው እየተከናወነ የሚገኘው:: በሁለት በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች የተጀመረው ይኸው ውድድር አሁን ላይ የመንግሥት እና የአካባቢው ወጣቶች ድጋፍ ታክሎበት በድምቀት በመካሄድ ላይ ይገኛል::

በከተማዋ በፊፋ ድጋፍ የሚንቀሳቀሱትን ጨምሮ በአጠቃላይ የጋሞ ጎፋ ዞን ውስጥ ትምህርት ቤቶችን አካቶ ከ28 በላይ ፕሮጀክቶች (ከ15 እስከ 20 ዓመት የሆናቸውን ታዳጊ ወጣቶች የያዙ) መኖራቸውን ኃላፊው ይጠቁማሉ:: ይሁንና በከተማዋ ካለው የእግር ኳስ እንቅስቃሴ አንጻር ይህም በቂ ሊባል አይችልም:: በርካታ በጎ ፈቃደኛ አሠልጣኞችም በስፖርቱ ላይ የራሳቸው ዐሻራ በማሳረፍ ላይ ቢገኙም ሥልጠናቸው በልምድ እንጂ በዘመናዊ ሥልጠና የተደገፈ አይደለም:: ይህም የነገ ተስፋ በሆኑ ታዳጊዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ እንደሚችል በመገንዘብ የእግር ኳስ አሠልጣኝነት ሥልጠናን እየሰጠ እንደሚገኝ ኃላፊው አስረድተዋል:: በዚህም በእውቀት የታነጸ፣ በአእምሮና በአካል ብቁ የሆነ ትውልድ ለማፍራት እንደሚያስችል ይታመናል::

በእግር ኳስ ስፖርት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያላት አርባ ምንጭ በብዙዎች አእምሮ ውስጥ ትዝታ ሆኖ በቀረው አንጋፋው ክለብ አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ይበልጥ




**የአርባ ምንጭ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ጌታ ሸታ፣**

ይታወሳል:: ፋብሪካው አሁን ላይ በመልካም ሁኔታ የሚገኝ እንደመሆኑ ክለቡ በድጋሚ እንዲመሠረት ጽሕፈት ቤቱ ንግግር በማድረግ በቀጣይ ዓመታት እውን ሊሆን የሚችልበት ፍንጭ ተገኝቷል:: የከተማዋ መለያ የሆነው አርባ ምንጭ ከተማ እግር ኳስ ክለብ ደግሞ ራሱን በገቢ እንዲችል እንዲሁም በስሩ የታዳጊ ክለቦችን በማቋቋም እንዲመጋገቡ በማድረግ ላይም በትኩረት እየተሠራ ነው:: ወደ አንደኛ ሊግ እንደሚያድግ ተስፋ የተጣለበት የአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ክለብም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ይጠበቃል:: ሌሎች ክለቦች ደግሞ በባለሃብቶች ድጋፍ የተመሠረቱ ቢሆንም በአቅምና በአደረጃጀት አንጻር ውስንነት ያለባቸው በመሆኑ ጽሕፈት ቤቱ ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል::

ከተማው የእግር ኳስ ስፖርት ማዕከል ይሁን እንጂ የሚመጥነው ስታዲየም የለውም:: እጅግ በተጎዳውና ያልተሟላ መሠረተ ልማት ያለው ሜዳው ጨዋታዎችን ለማድረግም ይሁን ደጋፊውን ለማስተናገድ አስቸጋሪ በመሆኑ በሕዝቡ በተደጋጋሚ ቅሬታዎች እንደሚነሱበት ይታወቃል:: በዚህም ላይ ከተማው ከሕዝቡ ጋር በመተባበር የፊፋን መስፈርት ያሟላ ሜዳ ለመገንባት እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል:: ግንባታው የተጀመረ ሲሆን፤ ሕዝቡ ተሳታፊ እንዲሆንም የማሳመን ሥራ እየተሠራ ነው:: ለምሳሌ ያህል ዘንድሮ 19 ክለቦች የተሳተፉበት የአንደኛ ሊግ ውድድር በከተማዋ አዘጋጅነት ሲካሄድ ከ18 ሚሊዮን ብር በላይ ከተማዋ ገቢ አግኝታለች፣ በመሆኑም ስፖርቱ ለአካባቢው ያለውን አስተዋፅዖ በማመላከትና ጥቅሙን በማሳየትም የሕዝቡን ተሳትፎ ለማሳደግ እየተሠራ ነው::

ከእግር ኳስ ባለፈ አካባቢው በአትሌቲክስ የሜዳ ተግባራት፣ ቦክስ እና መረብ ኳስ በመሳሰሉ ስፖርቶች እምቅ አቅም እንዳለው ይታወቃል:: ይሁን እንጂ በበቂ ሁኔታ እንዳልተሠራባቸው ኃላፊው ያምናሉ፤ ይህንንም ተከትሎ ከእግር ኳሱ ጎን ለጎን ውድድሮችን በማስፋፋት የላቁ ስፖርተኞችን የማፍራት ውጥን ይዘው እንቅስቃሴ መጀመራቸውንም ይጠቁማሉ:: በቅርቡ በከተማዋ የተካሄደው ታላቁ የአርባ ምንጭ ሩጫም በዚህ እንቅስቃሴ የራሱ ድርሻ እንደሚኖረውም ታምኖበታል::